# የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ጥር 2014 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ገጽ

1 ድረሞ........................................................................................................................ 3

2 መግቢያ ..................................................................................................................... 7

3 የሴክተሩ ዓላማ፡-............................................................................................................. 7

የሴክተሩ የትኩረት መስኮች እና የሚጠበቁ ውጤቶች............................................................................. 8

4. የሴክተር የልማት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች.................................................................................. 9

5 በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የአስር ዓመት የልማት (የፊዚካል) ዕቅድ አፈፃፀም ትንተና ..................................................................................................................... 11

2. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት መስኮች ፣ ግቦችና ዒላማዎች አፈጻጸም .................. 11

6. ሰንጠረዥ ........................................................................... Error! Bookmark not defined.

5) የተቋሙ የኦዲት ግኝት ምልከታ ................................................................................... 2

6 ) ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ............................................................. 2

7) ለክልሎች የተሰጠ የአቅም ግንባታ.............................................................................. 5

8) በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች.............................. 6

3. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች............................................................... 6

3.1. ያጋጠሙ ችግሮች ............................................................................................... 6

 ስራዎችን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል ፈጻሚውን እና አስፈጻሚውን ሊያሰራ የሚችል ምቹ የሆነ ቢሮ አለመኖሩ ፤............................................................................................ 6

3.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች.......................................................................................... 8

9) ማጠቃለያ (Conclusion) ........................................................................................ 8

**ድረሞ /Executive summary**

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር መስከረም/2014 የተደረገውን አዲስ የመንግስት ምስረታ ተከትሎ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የባህል፣ ኪነ-ጥበብ፣ ስነ-ጥበብ እና ፈጠራ እንዲሁም የስፖርት ዘርፍ ልማትን የተመለከቱ ስልጣንና ተግባራት ተሰጥተውት እንዲዋቀር ተደርጓል። ይህንኑ መነሻ በማድረግም የዘርፎቹን የፊዚካል እና የፕሮግራም በጀት ዕቅዶች ለአሠራር ምቹ በሆነ መልኩ በማዋሃድ ወጥ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል።ሴክተሩ የተቋቋመለትን አላማ መሰረት በማድረግ ከ10 አመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ውስጥ የ5 አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በመውሰድ የ2014 አመታዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በየዘርፉ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት  ቀርበዋል፡፡

በባህል ዘርፍ የኩሱሜ ቋንቋን ሰዋሰው የመጀመሪያውን ረቂቅ በብሄረሰቡ አባላት በማስተቸትና በማረም ለህትመት ዝግጁ ተደርጓል፡፡ 155 የቴአትር ትርዒት ኘሮግራሞችን ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 156 ትርኢቶችን ማቅረብ ተችሏል፡፡ 3 የብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ዜማዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 6 በማከናወን እቅዱን ከ100% በላይ መተግበር ተችሏል፡፡ ቀደም ሲል ሽፋን ያላገኙ 2 የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሙዚቃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 2 ተከናውኗል፡፡

ሁለት የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር መድረኮች ለማድረግ ታቅዶ አንድ በማከናወን የእቅዱን 50% ማከናወን ተችሏል፡፡ ከሀገር ሽማግሌዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በየአካባቢዉ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል 5 የውይይት መድረኮችን ለማካሄድ  ታቅዶ 5 መድረኮችን በማካሄድ የእቅዱ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ የንባብ ባህል ለማሳደግ 3 የህጻናት የንባብ ሳምንት ለማካሄድ ታቅዶ 2 በመከናወኑ አፈጻጸም 67% ሆኗል፡፡

የንባብ ባህል ሽፋንን በ21 ፐርሰንት ለማሳደግ ታቅዶ 18.5 ፐርሰንት ማሳደግ በመቻሉ አፈጻጸም 88% ሆኗል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የቤተመጽሐፍት የሪከርደና የቤተመዛግብት የተቀናጀ የአስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋትና ሥራ ላይ ለማዋል ይህንን ተግባር የሚያከናውን ሶፍትዌር በ32 ሚሊየን ብር ሶፍትዌሩን (Soutron) የሚባል

የውጪ እና ሜክ ኢንተርፕራይዝ (MAKE Enterprise) በሚባል አገር በቀል ድርጅቶች ለማልማት ታቅዶ የፕሮጀክቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ሶፍትዌሩ በሙከራ ትግበራ ላይ ይገኛል፡፡የዕደ-ጥበብ ምርቶችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ እና የእውቀት ሽግግር በማድረግ ምርታማነትን እና የገበያ ተደራሽነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 6 ወራት በዘርፉ ለሚገኙ ማህበራቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት ለዘርፉ ዕድገት ጠቃሚ በሆኑ አጀንዳዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

የጋምቤላ ባህላዊ የሉል ምርት (ሎል) እና የሀረሪ ክልል ሴቶች የባህል የአለላ ስፌት (ጌሞት) መለያ ብራንድ እንዲያገኙ የምርቶቹን ይዘት በማጥናት ረቂቅ የህግ ማዕቀፎችን የማዘጋጀት እና ሎጎዎችን የማስቀረፅ ስራዎች በማከናወን ምርቶቹ ለአዕምራዊ ንብረት ባለስልጣን እንዲቀርቡ ማድረግ ተችሏል።

በስፖርቱ ዘርፍም ንቁ፣ ተወዳዳሪ እና አሸናፊ ዜጋን ለመፍጠር ልዩ ልዩ የልማት ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን በየደረጃው የሚገኘውን የሕብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን ከመፍጠር አኳያ 1,261 መንግስታዊ ተቋማትን እና 122,904 ሕዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን ማደራጀት እና ማጠናከር ተችሏል።

በየደረጃው ስፖርቱን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው 7,431 የስፖርት ም/ቤቶች መደበኛ ጉባኤዎቻቸውን በማድረግ ለስፖርቱ ዕድገት ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎችን እና አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። በስፖርት ፖሊሲው በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ስፖርት ሕዝባዊ መሠረት እንዲይዝ የስፖርት አደረጃጀቶችን በቴክኒክ፣ በግብዓት እና በፋይናንስ የመደገፍ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ለሕዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች 78,204,654 የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል።

በስፖርት ልማት ዘርፍ በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት እንዲሁም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 232,745,762 ብር በማሠባሰብ የዘርፉን የፋይናንስ አቅም ማጎልበት ተችሏል። ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እና ሕጋዊ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በማስፋፋት ለሕብረተሰቡ ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ በትምህርት ቤቶች እና በተቋማት የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን 30,700 በማድረስ ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል። ከዚህ ውስጥም ሀገር አቀፍ ስታንዳርዱን የሚያሟሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ወደ 78 ማሳደግ ተችሏል። በተያያዘም በመላ ሀገሪቱ

የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ለሕብረተሰቡ ፍትሐዊ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የተደራሽነት መጠናቸውን 16% ማድረስ ተችሏል።

ሳይንሳዊ የስፖርት ትምህርትና ስልጠና አገልግሎት የሚሠጡ አዲስ እና ነባር የስፖርት ስልጠና ማዕከላትን 16 በማድረስ በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ እንዲጠናከሩ ማድረግ ተችሏል።ብቁ ተወዳዳሪ እና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት የሚሠጡ የስፖርት ባለሙያዎችን ለማፍራት ልዩ ልዩ የአሠራር ስርዓት ማሻሻያዎች እና ቅንጅታዊ ትብብሮች የተፈጠሩ ሲሆን ባለፉት

በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ፕሮግራሞች በዳኝነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በኢንስትራክተርነት እና በኮሚሽነርነት 2,634 ባለሙያዎች ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም 500 የስፖርት ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ /COC/ እንዲወስዱ ተደርጓል።

በሳይንሳዊ የስልጠና ዘዴዎች ተተኪ ስፖርተኞችን በማፍራት አሸናፊ ሀገርን ለመገንባት የተያዘውን ዓላማ ለማሳካት በመንግስት ድጋፍ 956 የታዳጊ ወጣቶች የስልጠና ጣቢያዎች እንዲከፈቱ የተደረገ ሲሆን በጣቢያዎቹ 23,900 ታዳጊዎች በ11 የስፖርት ዓይነቶች ስልጠናዎቻቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

**የስራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ** በባህል ዘርፍ ለ76,840 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 13,676 ዜጎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙ 18 በመቶ ደርሷል፣ በስፖርት ዘርፍ ለ3594 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ4,550 ዜጎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙ 100 በመቶ ደርሷል፡፡ በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት እና በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ህብረተሰቡን አስተባብረው 13,450,500 ብር በመሠብሰብ ስፖርቱን እንዲደግፉ ለማድረግ ታቅዶ 5,050,500 ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 93% ማሳካት ተችሏል፡፡ በስፖርት ዘርፍ 1,250,000ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 1,250,000ብር ገቢ ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

**በጀት አፈፃፀም** በሚኒስቴር መ/ቤት እና በተጠሪ ተቋማት የታቀዱ ስራዎችን በተያዘላቸው ጊዜና ወጪ ለማስፈፀም የሚያስችል የመደበኛ በጀት 420,458,932 ለመጠቀም ታቅዶ 180,694,548 ብር ስራ ላይ በማዋል አፈጻጸሙን 50 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በካፒታል በጀት 2,684,976,200 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 146,430,000 ብር ጥቅም ላይ በማዋል 57 በመቶ ማሳካት ተችሏል::

**በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻው** በወቅታዊው ሀገራዊ ቀውስ መንስኤነት አብዛኛዎቹ ተግባራት ባለመከናወናቸው በዋናው መ/ቤት ያሉ የስራ ክፍሎች፣ ተጠሪዎች፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአስቸኳይ የቀጣይ 6 ወር እቅድ በመከለስ ያልተከናወኑት ተግባራት እንዲካካሱ ሊረባረቡ የሚገባ መሆኑ ነው፡፡

- ☞ አዲስ የተዘጋጀው የሚኒስቴሩን መዋቅር ተግባራዊ በማድረግ መካከለኛውን አመራር እና የባለሙያውን ምደባ ማከናወን፣
- ⊙ የሚኒስቴሩን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በመከለስ እና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ በማስፀደቅ ወደስራ ማስገባት፣
- ⊙ ለክልሎችን/ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለተጠሪ ተቋማት የድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- ⊙ ለሚኒስቴሩ፣ ለክልሎች/ ከተማ አስተዳደሮች፣ ለተጠሪ ተቋማትና ለሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማጠናከር፣
- ⊙ የብሔራዊ ስታዲየም የምዕራፍ ሁለት ግንባታን እና የአዲስ አበባ ስታዲየም ዕድሳትና ጥገና በተያዘለት በጀትና መርሃ-ግብር መሰረት ጥገናውን አጠናቆ ወደስራ ማስገባት፣

## መግቢያ

በሀገራችን መስከረም 24/2014 ዓ.ም የተደረገውን አዲስ የመንግስት ምስረታ ተከትሎ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ስፖርት ዘርፎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተባብር እና የሚከታተል ተቋም "የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር" በሚል ስያሜ እንዲቋቋም መደረጉ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በስሩ ከሚገኙ ተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን አዲሱን የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም የሃገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የዘርፉን የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም የ2014 በጀት ዘመን ዕቅድን በማዋሃድ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ትኩረትና ክትትል የሚሹ፣ የማህበረሰቡን የአገልግሎት ጥያቄዎች የሚመልሱ ተግባራትን በአግባቡ የለየ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ርብርበ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በዚሁ መሰረት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ያካተተ የአፈፃፀም ሪፖርት በስምንት ክፍሎች እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በክፍል አንድ የሚኒስቴሩ ራዕይ፣ ተልዕኮ እንዲሁም ስልጣንና ተግባር፣ በክፍል ሁለት ዋና ዋና ቁልፍ ስራዎች አፈፃፀም፣ በክፍል ሦስት የ2014 በጀት ዓመት የአበይት ተግባራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በክፍል አራት የደጋፊ ስራ ሂደቶች ዕቅድ አፈፃፀም፣ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች፣ የፋይናንስና የሰው ኃይል ዕቅድ አፈፃፀም በክፍል አምስት ያልተከናወኑ ተግባራትና ምክንያቶቻቸው በክፍል ስድስት በአፈፃፀም ወቅት የታዩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች በክፍል ሰባት የክትትል የድጋፍና ግምገማ ሥርዓት እንዲሁም በክፍል ስምንት የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ሠንጠረዥ/Matrix/፣

## የሴክተሩ ዓላማ፡-

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብዝኃ-ባህላዊ ሀብቶችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ እና የማህበረሰብ ስፖርት በማስፋፋት ህብረተሰቡን በስፖርት እንቅስቀሴ በማሳተፍ ተወዳዳሪ የሰው ሃይል በመፍጠርና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ከዘርፉ የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ማሳደግ፡፡

### የሴክተሩ የትኩረት መስኮች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተዘጋጀውን የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እና የ5 ዓመቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የዘርፉ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የሚከተሉትን የትኩረት መስኮች ተለይተው በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

| ተ.ቁ | የትኩረት መስክ | ውጤት |
|---|---|---|
| 1. | ባህላዊ ሀብት ልማት | የተጠበቁ እና የለሙ ባህላዊ ሀብቶች |
| 2. | ብቁና ተወዳዳሪ ዜጋ | ጤንነቱ የተጠበቀ ተወዳዳሪ ዜጋ |
| 3. | የፈጠራ ኢንዱስትሪ ማጎልበት | የባህል ኢንደስትሪዉ የስራ እድል ለመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ፣ ሀገር ለመገንባትና የገር ሃይልን ለማጎልብት እንዲውል የሚያስችል ስርዓት መገንባት |
| 4. | የማህበረሰብ ተጠቃሚነትና አጋርነት | በተፈጠረ አጋርነት ተጠቃሚነቱ ያደገ ማህበረሰብ |
| 5. | የመረጃ ሥርዓት ልህቀት | የተሳለጠ የመረጃ ትንተና፣ ቅብብሎሽና አጠቃቀም |
| 6. | ተቋማዊ አቅም ግንባታ (Institional Building) | **ዘመናዊ ተቋማት መመሰረት ፣ ዘመናዊ አሰራሮችና ኦፕሬሽናል ስታንዳርዶችን መቅረጽ** |

## የሴክተር የልማት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች

በሴክተር ደረጃ የተዘጋጀው የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድና ከዚሁ የመነጨ የ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት በማድረግ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ታቅዶ በትግበራ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በትግበራ ወቅት የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት እና በቀጣይ ሊኖሩ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶችን በመዳሰስ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.1. የሴክተሩ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት

በዚህ የትኩረት አቅጣጫ ስር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በአጫጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ በዕውቀት እና በክህሎት ማብቃት፣
- የሴክተር ትራንስፎርሜሽን ወይም ለውጥ ማከናወን፣
- የአሰራር ማሻሻያዎች ማድረግ እና አዳዲስ ተጨማሪ ስትራቴጂዎች መቅረፅ
- አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣
- አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ተቋማትን መመስረት
- ሕዝባዊ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣
- የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ ማዘመን፣ ዘመናዊና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መተግበሪያዎችን /Application/ ማልማት
- የዘርፉ አደረጃጀት ሪፎረም ማከናወን፣
- የፖሊሲና የህግ ማሻሻያዎች ማከናወን፣
- የባህልና ስፖርት ሳተላይት አካውንት ማልማት፣
- ክልሎችን በአቅም ግንባታ ስልጠና ማጠናከር

### 1.2. የዘርፉ መሠረተ ልማት አቅርቦቶችን ማስፋፋት፣

ከግሉ ዘርፍ እና የልማት አጋሮች ጋር ቅንጅታዊ አሠራሮችን በመዘርጋት፡-

- የባህል ማዕከላትን ፣ ኤግዚቢሽን ማዕከላትን፣ ትያትር ቤቶች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ፊልም ቤቶችና፣

ሙዚየሞችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ምቹ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፤

- የተጀመረውን የዕደ-ጥበብ ማዕከል ማጠናቀቅ፤
- የባህል ማዕከላትን ዕድሳት ማጠናቀቅ፤

### 1.3. ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፣

ከተመረጡ ተዋናዮች ቅንጅታዊ አሠራሮችን ለማጠናከር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት በመስጠት መተግበር፡-

- ☞ ከሙያ ማህበራት ጋር ያለውን ትስስር ለማጠናከር የባህል ጥበባት ምክር ቤት መመስረት፤
- ☞ ከጥናትና ምርምር ተቋማት (ከመካነ ትምህርት ጋር ትስስርን ማስፋት)፤
- ☞ ከመያዶች ጋር ትስስርን ማስፋት፤
- ☞ የግል ዘርፉን ቁመና በአሰራር መደገፍና ማጠናከር፤
- ☞ በዘርፉ ያሉ አራቱን ተዋናዮች ማጠናከር እንዲሁም እርስ በእርስ ያላቸውን ትስስር ማጎልበት፤
- ☞ የሀገር ሀብትን በአግባቡ ሥራ ላይ ከማዋል አንፃር ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጎልበት፤
- ☞ የሰው ሀብት ልማት ማጠናከር፡፡

### 1.4. በዘርፉ ልማት ውስጥ የግል ዘርፉን ሚና ማሳደግ፣

በዚህ ርዕስ ስር ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፡-

- ☞ በዘርፉ የባለሀብቱን ተሳትፎ ማጎልበት፤
- ☞ አማራጭ የሥራ ዘርፎችን መለየትና እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፤
- ☞ የመንግስትን እና የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር፤

### 1.5. የኮቪድ 19 በዘርፉ ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቋቋምና እንዲያገግም ማድረግ

በዚህ ስር ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፡-

- ☞ ወረርሽኙን ተከትሎ የመጡ መልካም አጋጣሚዎች ለይቶ መጠቀም እንዲቻል ለተቋማት እና ለሙያተኛው ድጋፍ ማድረግ፤
- ☞ ወረርሽኙ በሴክተሩ (ዘርፎች) ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በአገር ደረጃ ማጥናትና መገምገም እና የተነደፉ የማገገሚያ ስትራቴጅዎች ተግባራዊ ማድረግ ፣

## በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የአስር ዓመት የልማት (የፊዚካል) ዕቅድ አፈፃፀም ትንተና

2. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት መስኮች ፣ ግቦችና ዒላማዎች አፈጻጸም

**<u>የትኩረት መስክ 1፡ ባህላዊ ሀብት ልማት</u>**

**ግብ 1፡ የብ/ብ/ህዝቦች የቋንቋዎች አጠቃቀምን ማጎልበት**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- ☞ የኩሱሜ ቋንቋን ሰዋሰው የመጀመሪያውን ረቂቅ በብሄረሰቡ አባላት በማስተቸትና በማረም ለህትመት ዝግጁ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡
- ☞ ለቤንሻንጉል፣ ለጋምቤላና ለድሬዳዋ ክልሎች የቋንቋና ሥነጽሁፍ ባለሙያዎች በቋንቋ ሰዋሰው አዘገጃጀት፣ በቋንቋና ሥነቃል ጥናትና ሥነዳ፣ በመዝገበ ቃላት ዝግጅት እና በትርጉም ዙሪያ የአሰልጣኞች ሥልጠና በመስጠት አቅም መገንባት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም የእቅዱ 75 በመቶ ነው፡፡
- ☞ ለሁሉም ክልሎች የባህል ኃላፊዎች በቋንቋ ፖሊሲ ይዘትና ስትራቴጂዎች ለማስተዋወቅ ዕቅድ ተይዞ በጸጥታ ችግር ምክንያት ከትግራይ፣አማራና አፋር ክልሎች በስተቀር ለሌሎች ክልሎች በአዳማ ከተማ የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ☞ ክልሎችም በራሳቸው መዋቅር ለሚመከለታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ የቤት ስራ ወስደዋል፡፡ በአዲሱ የደቡብ ምዕራብ ክልል በሚዛን ከተማ ከኤስ አይ ኤል- ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በጠቅላላው 250 ተሳታፊዎች በተገኙበት ፖሊሲውን ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡

- የቋንቋ ፖሊሲን ለፌዴራል የስራ ቋንቋነት እንዲውሉ በፖሊሲው እውቅና በተሰጣቸው አራት ቋንቋዎች (ኦሮምኛ፣ ሶማሊኛ፣ አፋርኛና ትግርኛ ቋንቋዎች በማስተርጎም ለማሳተም ታቅዶ በኦሮምኛና ሶማሊኛ ተተርጉሞ ለህትመት የተዘጋጀ ሲሆን በአፋርኛ ለማስተርጎም በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት የዘገየ ቢሆንም በአሁኑ ሠዓት እየተተረጎመ ይገኛል፡፡ የትግርኛ ቋንቋ ትርጉም ባለው ወቅታዊ ችግር ምክንያት ማስተርጎም አልተቻለም፡፡ አፈጻጸሙም 75 በመቶ ነው፡፡

**ግብ 2፡ የብሄር ብሄረሰቦች የስነ- ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማጎልበት**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- 250,000 በኪነጥብብ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማቅረብ ታቅዶ 261,666 ህብረተሰብ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡
- 155 የቴአትር ትርዒት ኘሮግራሞችን ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 156 ትርኢቶችን ማቅረብ ተችሏል፡፡ እነዚህም በመደበኛ፣ በአዘቦትና በእሁድ ቀንቤቀረቡ ቴአትሮች ሲሆኑ ዝርዝሮቹም “የእኛ ሰፈር”፣ “የኮከቡ ሰው”፣ “አልቃሽ እና ዘፋኝ”፣ “ባቢሎን በሳሎን”፣ “ሩብ ጉዳይ” እና ‹‹እያዩ ፈንገስ ቁ.2 ›› ናቸው፡፡
- የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ 82 የሙዚቃ ትርዒቶችን በማእከል፣ በክልል እና በውጭ ሀገራት ለሕዝብ ለማቅረብ ታቅዶ 50 (2 የበኣላት ሙዚቃ ትርኢት፣ 16 የባህል ሙዚቃ ትርኢት፣ 9 የዘመናዊ ሙዚቃ ትርኢት) በማቅረብ የእቅዱ 61% ተፈፅሟል፡፡
- በኪነጥበብ ኢንተርፕራይዞች፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች የሚቀርቡ 34 የአዳራሽ ዝግጅቶችን ለማስተናገድ ታቅዶ 48 ዝግጅቶችን በማስተናገድ አፈጻጸሙ 100% ደርሷል፡፡
- 3 የብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ዜማዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 6 በማከናወን አፈጻጸሙ 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- ቀደም ሲል ሽፋን ያላገኙ 2 የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሙዚቃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 100% ተከናውኗል ፡፡
- ልማታዊ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው በመድረክ፣ በሬድዮና ቴሌቪዥን የሚቀርቡ 4 ዝግጅቶችን ለማቅረብ ታቅዶ 7 በማከናወን እቅዱን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ ስራውም ከመከላከያ ጎን መቆምን የሚያበስርና የሚቀሰቅስ ህብረ ዝማሬ በሶሻል ሚዲያና በመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ እንዲሆን ማድረግን የሚያካትት ነው፡፡

- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጁ 9 አዳዲስ ዘመናዊ የሙዚቃ ዜማዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 11 በማከናወን የእቅዱ 100% ተፈጽሟል ፡፡
- 1 አዲስ የአዘቦት እና የሙሉ ቀን የቴአትር ጥበብ ሥራ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 "የሰይጣን- ባቡር" የተሰኘ የአዘቦት ቀን ቴአትር በዝግጅት ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡

**የትኩረት መስክ 2፡ የፈጠራ ኢንዱስትሪ ማጎልበት**

**ግብ 3: የዕደ-ጥበብ ምርትን ማሰፋፋትና ገበያን ማጎልበት**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- 2 የእደጥበብ ምርቶችን የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር መድረኮች ለማድረግ ታቅዶ 1 በማከናወን የእቅዱን 50% ማከናወን ተችሏል፡፡
- የባህል ምርቶች መለያ (ብራንድ) ሰነድ ለማዘጋጀት እና ብራንድ ለማሰጠት በታቀደው መሰረት በጋምቤላ ክልል የሚገኝ የሉል ምርትን ብራንድ እና በሀረሪ ክልል የሚገኘውን ጌሞት (የአለላ ስፌት) መለያ ለማሰጠት ጥናት በማካሄድ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለብራንድ ዝግጅት የሚያስፈልገው ስራ ተሰርቶ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በማቅረብ ክትትል እየተደረገበት ይገኛል የእቅዱም 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

**ግብ 4: *የዕይታዊ፣ ትዕይንታዊ እና ሰነ-ፅሁፍ ጥበባት ኢንዱስትሪን በማጎልበት የዉጭ ገበያ ተደራሽ ማድረግ፣***

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የ2013 ዓ.ም የሽልማት ሂደት አፈጻጸም ሁሉም የሙያ ማህበራት በተገኙበት በመገምገም ለ2014 ሽልማት ሂደት ከማህበራት በተጨማሪ የግል የሽልማት ሥራ ደርጅቶች የሚካተቱበትን ሁኔታ በማጥናት መመሪያውን ለመከለስ እንዲቻል የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፣ ጥናቱን መሰረት ያደረገ የመመሪያ ክለሳ ለማከናወን የማስፈጸሚያ እቅድም ተዘጋጅቷል፡፡
- የግል የሽልማት ሥራ ደርጅቶች ማሳተፍ የሚያስችል ማእቀፍ ሪቂቅ ተዘጋጅቷል አፈጻጸሙ 60% ነው፡፡

**ለፊልም ፖሊሲ ማስፈፀሚያ የተዘጋጀ ስትራቴጂ**

- በ2010 ዓ.ም በመንግስት ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለው የኢትዮጵያ ፊልም ፖሊሲን ለማስተግበር የሚረዳ የሕግ ማዕቀፍና የስትራተጂ ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ (የሀገር

ውስጥና ዓለም አቀፍ ሙያተኞችን በመመደብ) ከዩኔስኮ በተገኘው ድጋፍ ሀገር አቀፍ ግብረ ሃይል ተቋቁሞ ሥራው የተጀመረ መሆኑ፡-

እስከ አሁን የተከናወኑ ተግባራትም፡፡

- ☞ በግብረ ሃይሉ ለፊልም ተቋም ምስረታ የሚሆን ተቋማዊና ሕጋዊ የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅት የሚረዱ ዳሰሳ ጥናቶች ተከናውኗል፣
- ☞ የማእቀፎቹ ረቂቅ ለባለድርሻ አካላት በበይነ መረብ ውይይት ተደርጎበት ግብአት ተሰብስቧል፣
- ☞ ግብአት የተሰበሰበበት የማእቀፎቹ ሁለተኛ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፣
- ☞ ለፖሊሲ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ ስትራተጂ ዝግጅት የሚሆን የጥናት ሥራ ውል ዩኔስኮ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመዋዋል ለጥናት ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

**የተሻሻሉ የባህል ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ስትራቴጂዎች እና አሰራር ስርአት ሰነዶች ዝግጅት**

- ✍ ለሶስት የአሰራር ስርአት ሰነዶች፣ ለሁለት የደንብ ሰነድ እና አንድ መመሪያ ሰነድ የማዳበር ሥራ ዝግጅቶች ተከናውኗል

**የህዝቦችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠናክር ሙዚቃዊ ትርኢት (ድንቅነሽ ኢትዮጵያ) መድረኮች ማካሔድ**

- ✍ ትርኢቱን ለማስተባበር ለተመረጡ አሰልጣኝ ሙያተኞች ስራውን እንዲጀምሩ አሰፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፣
- ✍ የልምምድ ተግባሩ እንዲጀመር የትርዒቱ ዝግጅት የድርጊት መርኃ ግብር እና የማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፣
- ✍ ለተመደቡ ባለሙያዎችና አስተባባሪዎች ቢሮና የመለማመጃ ቦታዎችን ተመቻችቷል፣

**ከሙያ ማህበራት ጋር በዕቅድ እና ልዩ ልዩ አፈፃፀም የተደረጉ ምክክሮች**

- ✍ ከሙያ ማህበራት ጋር በዕቅድ እና ልዩ ልዩ አፈፃፀም ጉዳዮች አንድ የምክክር መድረክ ተከናውኗል፡፡

**ግብ 5: የባህል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማጎልበት ገበያን ማስፋፋት**

- ☛ በዚህ ግብ ስር ታቅደው የነበሩ ተግባራት ምንም አይነት ስራ አልተከናወነም፡፡

**ግብ 6: አገር በቀል እውቀቶችን በመጠበቅ ማልማት**

<u>**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**</u>

- ከሀገር ሽማግሌዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶች በማድረግ 5 በየአካባቢዉ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ በመፍታት ያደገ አቅምን ለመፍጠር 5 የውይይት መድረኮችን በማካሄድ የእቅዱ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

**ግብ 7፡ የትውፊታዊ ሀብቶች እና ማህበራዊ እሴቶች ለህዝቦች ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ትስስር ያላቸውን ሚና ማሳደግ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- 12ኛው ሀገር አቀፍ የመቻቻል ቀን "መቻቻል ለሰላም፣ ለአብሮነትና ለጋራ እድገት" በሚል መሪ ቃል ለማክበር ታቅዶ 1 በማከናወን አፈፃጸሙ 100% ነው፡፡

- የመስቀል በአል የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት 1 ታቅዶ 1 በማከናወን አፈፃጸሙ 100% ነው፡

**ግብ 8: የእውቀት አሰተዳደርና መረጃ ማህበረሰብ የመፍጠሩን ስራ ማጎልበት**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- የንባብ ባህልን ለማስፋፋት 7 የንቅናቄ ፕሮግራሞችን ለማካሄድ ታቅዶ 6 የንቅናቄ ፕግራሞችን በማከናወን የዕቅዱን 86% ማሳካት ተችሏል፣
- **የንባብ ባህልን ለማስፋፋት** 3 የንቅናቄ ፕሮፕራሞች ለማካሄድ ታቅዶ 2 የህጻናት የንባብ ሳምንት በመከናወኑ አፈጻጸም 67% ሆኗል፡፡
- የንባብ ባህል ሽፋንን በ21 ፐርሰንት ለማሳደግ ታቅዶ 18.5 ፐርሰንት ማሳደግ በመቻሉ አፈጻጸሙ 88% ሆኗል፡፡
- **<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**
- 1,967,322 ህብረተሰብ ክፍል የንባብ አገልግሎት ለማዳረስ ታቅዶ 1,742,235 የህብረተሰብ ክፈሎች የንባብ አገልግሎቱን የማዳረስ ስራ ተከናውኗል፡፡
- 43,779 የመረጃ ሀብቶችን በማሰባሰብ ክምችት ለማሳደግ ታቅዶ 40,841 በመሰባሰቡ አፈፃፀም 93% ተከናውኗል፡፡

- 38,499 የመረጃ ሀብቶችን በሳይንሳዊ ዘዴ በማደራጀት ለአገልግሎት ለማብቃት ታቅዶ 41,056 በመደራጀቱ አፈፃጸም 100% ሆኗል፡፡

- ለ 14,555 የመረጃ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ ለ 18,235 የመረጃ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ በመደረጉ አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡
- ከአንድ መዛግብት ሊያዛውር ከሚችል የፌዴራል የመንግስት መ/ቤት ጋር በሪከርድ ምዘናና መረጣ ላይ በጋራ ለመሥራት ታቅዶ በዕቅዱ መስረት በመከናወኑ አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡
- 600 የውዝፍ ሪከርዶች ምዝገባ፣ የምዘናና መረጣ እና የመለያ ቁጥር የመስጠት ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 483 በመከናወኑ አፈጻጸም 81% ሆኗል፡፡
- አንድ የጽሑፍ ቅርስ በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ዲስክሪፕሽን በማዘጋጀ ለመላክ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት በመከናወኑ አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡
- 12ቱን የፅሁፍ ቅርሶች ለ900 ሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ለማስጎብኘት ታቅዶ 986 የጎበኙ ሲሆን አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡
- 12ቱን የፅሁፍ ቅርሶች ለ30 የውጭ ጎብኝ ቱሪስቶች ለማስጎብኘት ታቅዶ 35 የጎበኙ ሲሆን አፈፃፀም 100% ሆኗል፡፡

**ግብ 9: የዘርፍ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት**

- በባህል ጥበባት ሥራዎች ለሚሰሩ ባለሃብቶች የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

**ግብ 10፡ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ ማዘመንና ማሻሻል**

- የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የቤተመጽሐፍት የሪከርደና የቤተመዛግብት የተቀናጀ የአስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋትና ሥራ ላይ ለማዋል ይህንን ተግባር የሚያከናውን ሶፍትዌር በ32 ሚሊየን ብር ሶፍትዌሩን (Soutron) የሚባል የውጪ እና ሜክ ኢንተርፕራይዝ (MAKE Enterprise) በሚባል አገር በቀል ድርጅቶች ለማልማት ታቅዶ የፕሮጀክቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ሶፍትዌሩ በሙከራ ትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

**ግበ 11. የህዝባዊና እና መንግስታዊ ስፖርት አደረጃጀቶችን በመፈተሽ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የስፖርት ተቋማትን ቁጥር ማሳደግ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- በየደረጃው 1250 የስፖርት ም/ቤቶችን እንዲካሄዱ ለማድረግ ክትትልናድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 760 ምክር ቤቶች በክልል/ከተማ አስተዳደሮች፣ በዞን/ክፍለ ከተማ፣በወረዳዎች እንዲሁም በቀበሌዎች ደረጃ በመካሄዳቸው አፈፃፀሙ 61% ላይ ይገኛል፣
- 15,720 የስፖርት ምክር ቤት ለማቋቋም ታቅዶ 7,431 በማከናወን የእቅዱን >100% ማከናወን ተችሏል፣
- በየደረጃው 100 ያክል መንግስታዊ የስፖርት ተቋማትን ለማጠናከርና ለመደገፍ ታቅዶ 89ተቋማትን መደገፍና መከታተል በመቻሉ አፈፃፀሙ 89 % ላይ ይገኛል፣
- 1,321 መንግስታዊ የስፖርት ተቋማትን ለማደራጀትና ለመደገፍ ታቅዶ 1,261 በማከናወን የእቅዱን 95.5% ማከናወን ተችሏል፣
- ከፌደራል እስከ ቀበሌ 128,676 ሕዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን ማለትም (የስፖርት ማህበራት፣ የስፖርት ክለቦች፣ የስፖርት ቡድኖች፣ የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴዎች፣ የስፖርት ህክምና ኮሚቴዎች እንዲሁም የስፖርት ሙያ ማህበራት) እንዲደራጁ እና እንዲጠናከሩና እንድደገፉ ለማድረግ ታቅዶ 122,904 ያክሎቹን በተለያዩ ዘደዎች መደገፍ በመቻሉ አፈፃፀሙ 95.5% ላይ ይገኛል፣
- 128,676 ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 122,904 በማከናወን የእቅዱን 95.5% ማከናወን ተችሏል፣
- በየደረጃው ካሉ የስፖርት ዘርፍ ማለትም የሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ከተለያዩ ምንጮች ከክልሎችናከተማ አስተዳደሮች ከህብረተሰቡ ጭምር 133,400,000 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ አጋር ተቀማቶች ገቢ ማሰሳሰብ የተቻለ ሲሆን በዚህም 115,733,154 ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 86.8 % ላይ ይገኛል፣
- በአጠቃላይ በ6 ወሩ 246,500,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 239,622,630 ብር ገቢ በማሰባሰብ የእቅዱን 97.2% ማከናወን ተችሏል፣
- ቀደም ሲል በፌደራል ደረጃ የተዘጋጁና ፀድቀው ስራ ላይ የሚውሉ 7 የህግ ማዕቀፎችንና ስታንዳርዶችን በማጠናቀቅ የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት በተያዘው ዕቅድ መሰረት፡-
    - የስፖርት ፖሊሲ/ ክለሳ፣

▪ ረቂቅ የስፖርት አዋጅ/ኮድ/ህግ ዝግጅት

▪ የሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የተሻሻለ መመሪያ፣

▪ የስፖርት ማህበራት የውጤት አመልካችና መመዘኛ ሰነድ፣

▪ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች የአስተዳደር፣ የአጠቃቀም እና የአጠባበቅ ማንዋል

▪ የስፖርት ልማት ፈንድ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ከተዘጋጁት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ለባለድርሻ አካላት ቀርበው ግብዓት እንዲሠጥባቸው በማድረግ የተወሰኑት ወደስራ የገቡ ሲሆን ሌሎቹን በሚመለከታቸው አካላት አፀድቆ ወደስራ የማስገባት ሒደት ላይ ይገኛሉ፡፡

- 7 የህግ ማዕቀፍ አፀድቆ ተግራዊ ለማድረግ ታቅዶ 5 ያክሉ በመከናወናቸው አፈፃፀሙ 71.4% ላይ ይገኛል፣
- በየደረጃው ለሚገኙ ስፖርት ማህበራት 30,951,850 መንግስታዊ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በፌዴራልና በየክልሎች ደረጃ ለሚገኙ ህዝባዊ አደረጃጀቶች በድምሩ 19,443,485 ብር ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙን 63% ማድረስ ተችሏል፣
- በአጠቃላይ 61,902,200 ብር ለመደገፍ ታቅዶ 64,671,850 ብር በመደገፍ የእቅዱን >100% ማከናወን ተችሏል፣

**ግብ 12. የስፖርት ማዝወተሪያ ስፍራዎች በማሳደግ ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥና ተደራሽ ማድረግ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- የእውቅና ማረጋገጫ እና ካርታ ያላቸው ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር 29,500 ወደ 38,688 ለማሳደግ ታቅዶ አፈፃፀሙ 30,700 በማድረስ የዕቅዱን 79% ማሳካት ተችሏል
- ሀገር አቀፍ ስታንደርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ቁጥር ወደ 107 ለማድረስ ታቅዶ 78 በማከናወን የዕቅዱን 73% ማከናወን ተችሏል፣
- በትምህርት ቤቶችና እና በተቋማት ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር 29,500 ወደ 38,688 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ 30,700 በማድረስ የዕቅዱን 79% ማሳካት ተችሏል፣

- የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ተደራሽነት 17% ለማድረስ ታቅዶ 16% በማድረግ የዕቅዱን 94% ማሳካት ተችሏል፣
- ስታንዳርዱን በጠበቁ ቁሳቁሶች ተሟልተው አገልግሎት የሚሠጡ የስፖርት ስልጠና ማዕከላትን ቁጥር 17 ለማድረስ ታቅዶ 16 ማሠልጠኛ ማዕከላት በሰው ኃይልና በግብዓት ተሟልተው አገልግሎት እንዲሠጡ በማድረግ የዕቅዱን 94% ማከናወን ተችሏል፣

**ግብ 13 በየደረጃው የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርን በማስፋፋት የሚሳተፈውን ህብረተሰብና ተሳትፎ ሽፋኑን ማሳደግ**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የህብረተሰቡ የጤናና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ተሳትፎ 20% ለማድረስ ታቅዶ 18% ማድረስ ተችሏል፣
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ ት/ቤቶች የጤናና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት የሚሳተፈውን ሕብረተሰቡ በሚሠራበት ስፍራዎች የጤናና የአካል ብቃት እንቅስቃሴን በማስፋፋት በመስሪያ ቤቶች በጤናና በአካል ብቃት የሚሳተፈውን የሕብረተሰብ ክፍል ማሳተፍ ተችሏል፣
- ህብረተሰቡ በሚኖርበት ስፍራዎች በጤናና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን ማሳተፍ ተችሏል፣
- ደንቦችና የጨዋታ ህጎች በወጥቶላቸው ባህላዊ ስፖርቶች ህብረተሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፣
- በተዘጋጁ የባህል ስፖርት ፌስቲቫሎችና ኩነቶች ህብረተሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፣

**ግብ 14. የኢሊት (የአዋቂ እና የላቀ) ስፖርተኞችን ቁጥር ማሳደግ**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ልማት ፕሮግራም ለውጤታማነት ሊያግዙ የሚችሉ የማሰልጠኛ ማንዋሎች ማስተዋወቅ እና በስልጠና አሰጣጥ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር የሚያስችል ዙሪያ መድረክ ተዘጋጅቷል፣
- የታዳጊ ወጣቶች የስልጠና ፕሮግራም አካል የሆኑ ባለድርሻ አካላትን በማስተሳሰር የሚተገበር ሀገራዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት የሚያስችሉ 3 ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፣

- በመንግስት ማበልፀጊያ ማዕከላት የተሻለ ብቃት ያላቸው ሰልጣኞችን ቁጥር 2,516 ለማድረስ ታቅዶ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ 271፣ በጥሩነሽ ዲባብ ስፖርት ማሰልጠኛ 340፣ በየክልሎች ባሉ ማሰልጠኛዎች 1,596 በአጠቃላይ 1,692 ሰልጣኞች ስልጠና እንዲከታተሉ በማድረግ የዕቅዱን 67% ማከናወን ተችሏል፣
- በየደረጃው በመንግስት ድጋፍ 1,000 የስልጠና ጣቢያዎች ተከፍተው ስልጠና እንዲሠጡ ለማድረግ ታቅዶ 956 የስልጠና ጣቢያዎችን በመክፈት የዕቅዱን 95.6% ማከናወን ተችሏል፣
- በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ለ1,315 የስፖርት ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት በዳኝነት እና በአሰልጣኝነት ስልጠና ለ1,284 ወይም 97.6% ማከናወን ተችሏል፣

በአጠቃላይ 4,014 የስፖርት ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 2,530 በማከናወን የእቅዱን 63% ማከናወን ተችሏል፣

**ግብ 15 በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በልዩ ልዩ የስፖርት ዓይነቶች በመሳተፍ ውጤት ማስመዝገብ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- 30 ሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ብሄራዊ ቡድን እንዲያዘጋጁ ታቅዶ 26 ማዘጋጀት በመቻሉ የዕቅዱን 86.7% ማከናወን ተችሏል፣
- በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ በ8 የስፖርት አይነቶች ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በ5 የስፖርት ዓይነቶች መሳተፍ በመቻሉ የዕቅዱን 62.5% ማከናወን ተችሏል፣
- በአፍሪካ ሻምፒዮና በ7 የስፖርት ዓይነቶች ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በ4 የስፖርት አይነቶች በመሳተፍ የዕቅዱን 57% ማከናወን ተችሏል፣
- በኦሎምፒክ መድረክ በ6 የስፖርት ዓይነቶች ለመሳተፍ ታቅዶ በ4 ስፖርት (በአትሌቲክስ ስፖርት፣ በካራቴ፣ በውሃ ዋና እንዲሁም በብስክሌት ውድድር) በመሳተፍ የዕቅዱን 66.7% ማሳካት ተችሏል፣
- በአህጉርና አለም አቀፍ የውድድር መድረኮች በ11 የስፖርት አይነቶች ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በ9 የስፖርት ዓይነቶች (እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ወርልድ ቴኳንዶ፣ ብስክሌት፣ ውሃ ዋና፣ ፓራሊምፒክ፣ ቮሊቦል፣ ቼዝ እና ቦሊንግ ስፖርቶች) ተሳትፎ በማድረግ የዕቅዱን 81.8% ማሳካት ተችሏል፣

- በምስራቅ አፍሪካ፣ በአፍሪካ እና በኦሎምፒክ ደረጃ በ4 የስፖርት ዓይነቶች ውጤት እንዲመዘገብ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ5 የስፖርት አይነቶች (እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ወርልድ ቴኳንዶ፣ ፓራሊምፒክ እና ቼዝ ስፖርቶች) ውጤት በማስመዝገብ የዕቅዱን 66.7% ማሳካት ተችሏል፣
- በ32ኛ ቶኪዮ ኦሎምፒክ ጨዋታ 4 የስፖርት ዓይነቶች ውጤት ለማስመዝገብ ታቅዶ በአትሌቲክስ አንድ ወርቅ፣ አንድ ብር እና 2 የነሐስ ሜዳሊያ እንዲሁም በወርልድ ቴኳንዶ ዲፕሎማ በማስመዝገብ የዕቅዱን 50% ማሳካት ተችሏል፣
- በቶኪዮ በተካሔደው የ16ኛው ፓራሊምፒክ ጨዋታ በፓራ አትሌቲክስ ስፖርት በመሣተፍ አንድ ወርቅ እና ሁለት ዲፕሎማ በማስመዝገብ ውድድሩን ማጠናቀቅ ተችሏል፣
- በምስራቅና መካከለኛዉ አፍሪካ ጨዋታ U-20 የሴቶች ብሄራዊ ቡድን በሁሉም ጨዋታዎች ከፍተኛ ጎል በማስቆጠር የውድድሩ አሸናፊ መሆን የተቻለ ሲሆን ሃገራችን የዋንጫና የሜዳሊያ ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፣
- በዓለም ዓቀፍ እና አህጉር አቀፍ የስፖርት ውድድር መድረኮች ላይ በበጀት ዓመቱ 6 ወራት 200 አትሌቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 280 አትሌቶችን (እግር ኳስ፣ አትሌቲክስ፣ ወርልድ ቴኳንዶ፣ ብስክሌት፣ ውሃ ዋና፣ ፓራሊምፒክ፣ ቮሊቦል፣ ቼዝ እና ቦሊንግ ስፖርቶች) በማሳተፍ የዕቅዱን >100% ማከናወን ተችሏል፣

**በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስተናገድም**

- የሴካፋ ከ23 ዓመት በላይ የዕግር ኳስ ውድድርን በሃገራችን በባህር ዳር ከተማ በደማቅ ሁኔታ ማዘጋጀት ተችሏል፣
- የአፍሪካ ዊልቸር ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽኖች በሁለቱም ፆታ ለአለም ዋንጫ ለማለፍ የሚያደርጉትን የማጣሪያ ውድድሮች በሃገራችን ለማስተናገድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ማጠናቀቅ ተችሏል፣

**ግብ 16 የተዘጋጁ ሀገር አቀፍ የውድድር መድረኮችን ማሳደግ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- ካራቴ ፌዴሬሽን እና ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን የብሄራዊ ቡድን ማጣሪያ ማከናወን የቻሉ ሲሆን 3 ሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ማለትም ጠረጴዛ ቴኒስ፣ እግር ኳስ እና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውድድሮችን ማካሄድ ችለዋል፡፡

- በመሆኑም 5 ሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ውድድር እንዲያከናውኑ ታቅዶ 3 በመፈፀም የዕቅዱን 60% ማሳካት ተችሏል፣ እንዲሁም በ6 ወሩ 8 ሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ውድድር እንዲያከናውኑ ለማድረግ ታቅዶ 4 በማከናወን የዕቅዱን 50% ማከናወን ተችሏል፣
- ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በፀረ-ዶፒንግ ዙሪያ ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን በስፖርት አበረታች ቅመሞች ዙሪያ ውድድር ግዜና ከውድድር ውጪ ለ130 አትሌቶች የደም፣ የሽንትና (ABP) የአበረታች ቅመሞች ምርመራ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ ለ182 አትሌቶች ምርመራ በማድረግ የዕቅዱን >100% ማከናወን ተችሏል፣
- በአጠቃላይ ለ400 ስፖርተኞች በስፖርት አበረታች ቅመሞች የደም፣ የሽንትና ABP ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ329 በማከናወን የእቅዱን 82.3% ማከናወን ተችሏል፣
- በ33ኛው የካሜሩን 2022 የእግር ኳስ የወንዶች ብሄራዊ ቡድን የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር እንዲሁም ለዓለም ዋንጫ ማጣሪያ (በሁለቱም ፆታዎች) በመሳተፍ ውጤት እንዲመዘገብ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር ክትትል እና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፣

**ግብ 17 የስፖርት ማህበራዊ ልማትና ዲፕሎማሲን ማሳደግ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- በሀገር አቀፍ ደረጃ ስፖርትን ለማህበራዊ ልማት የሚጠቀሙ ተቋማትን ብዛት 34 ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ በበጀት ዓመቱ 6 ወራት 24 በማድረስ የዕቅዱን 71% ማከናወን ተችሏል፣
- ከፌደራል እስከ ቀበሌ በስፖርት ለማህበራዊ ልማት ላይ የሚሰማሩ የሲቪክ ማህበራትን ብዛት 20 ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ በበጀት ዓመቱ 6 ወራት 14 ተቋማት በስፖርት ለልማት እንዲሳተፉ በማድረግ የዕቅዱን 70% ማከናወን ተችሏል፣
- በበጀት ዓመቱ 6 ወራት ከፌደራል እስከ ቀበሌ በስፖርት ለልማት (በትምህርት፣ በጤና እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊ ልማቶች) 5,000 አካል ጉዳተኞችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 3,500 አካል ጉዳተኞችን ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ የዕቅዱን 70% ማከናወን ተችሏል፣

- ከፌደራል እስከ ቀበሌ በስፖርት ለልማት ስራዎች በ6 ወሩ 50,000 ሴቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 32,100 ሴቶችን በስፖርት ለልማት ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ዕቅዱን 64% በላይ ማከናወን ተችሏል፣
- ከፌደራል እስከ ቀበሌ የስፖርቱን ማህበረሰብ በማንቀሳቀስ በማህበራዊ ልማት ስራዎች በ6 ወሩ 5,196 በጎ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 4370 የስፖርት ማህበረሰብ በበጎ ፈቃደኝነት በመሰማራት ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎት መስጠት የቻሉ ሲሆን የዕቅዱን 84% ማከናወን ተችሏል፣

**ግብ18፡ የዘርፈን መረጃና የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማጎልበት/የመረጃ አሰባሰብ አያያዝ አጠቃቀምና አሰረጫጨት ስርዓትን ማጎልበት**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- 40 አዳዲስ መረጃዎችን በቴአትር ቤቱ ዌብሳይት /ድረ-ገጽ/ ለመጨመር ታቅዶ 48 በመፈጸሙ እቅዱን ከ100% ማከናወን ተችሏል፡፡
- በፌዴራል ደረጃ እንዲሁም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የስፖርት ልማቱን ሊያሳድጉ እና ሊያዘምኑ የሚችሉ 8 የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 8 የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማለትም የዕድሜ መመርመሪያ መሳሪያዎች/MRI/፣ የልብ መመርመሪያ /ECG/፣ የኦንላይን ምዝገባ /online registration/፣ የዳኞች መገናኛ መሣሪያዎች፣ ፎቶ ፊኒሽ ካሜራ፣ video assistant referee (VAR)፣ እንዲሁም virtual running app. በስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የDatabase system and sport portal ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፣
- ዘመናዊ የአትሌቲክስ ስፖርት ማወዳደሪያ መሳሪያ (timetronics)
- ከ8,000,000,ብር በላይ ወጭ በማውጣት በግዥ ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት የተቻለ ሲሆን በቴክኖሎጂው አጠቃቀም ዙሪያ ለ 23 ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል፣
- የCECAFA U-23 challenge cup ሙሉ ዉድድሩን ሶፍትዌር በማበልጸግ ዉጤቶችን እና መርሀ-ግበሮችን ለመላዉ ዓለም በሲስተሙ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፣

- የኢትዮጲያ ስፖርት ፖርታልን በአዲስ መልኩ በማሻሻል እና በማስተካከል ቪዲዮ እና ፎቶዎችን እንዲቀበል ማድረግ ተችሏል፣

**የትኩረት መስክ 5: ተቋማዊ አቅም ግንባታ (Institional Building)**

**ግብ 19፡ የዘርፈን የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማጎልበት**

## የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- አንድ የተገልጋዮች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 1 በመከናወኑ አፈጻጸም 100% ነወ፡፡
- በዘርፉ 8 የጥናት እና ምርምር ስራዎችን በበጀት ዓመቱ 6 ወራት ለማከናወን ታቅዶ በስፖርቱ ዘርፍ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፤በክልሎች ጭምር 10 የተለያየ ደረጃ ያላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች እየተካሄዱ ሲሆን በሂደት ላይ በመሆናቸው አፈፃፀማቸው 50% ላይ ማድረስ ተችሏል፣
- የዘርፉን የጥናትና ምርምር ስራዎች ለማጠናከር እና የሰው ሀብቱን ለማልማት የሚያስችል ተቋም ለመገንባት የሚያስችሉ የቅድመ-ዝግጅት ስራዎችን ማከናወን ተችሏል
- አንድ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 1 በመከናወኑ አፈጻጸም 100% ነው፡፡
- አንድ የፋይዳ ግምገማ ስልጠና ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ የጥናቱ 0.99 በመስራቱ አፈጻጸም 99% ነው፡፡
- አንድ የህዝብ ቤተመጽሀፍት ያለበት ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ የጥናቱ 0.93 በመሰራቱ አፈጻጸም 93% ነው፡፡
- 2 ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮ ሥራዎች(የቴአትርና የሙዚቃ) ለማጥናት ታቅዶ 2 በማከናወን የእቅዱ 100 % ነው፡፡

**ግብ 20፡ የዘርፉን የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማጎልበት**

## የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ☛ በሪከርድ ሥራ አመራር፣ በመዛግብት አስተዳደር እና በቤተመጻሕፍት ሙያዎች ላይ በመደበኛ መርሀግብር 165 ሙያተኞች ለማሰልጠን ታቅዶ 151 በመሰልጠናቸው አፈጻጸም 92% ነው፡፡
- ☛ ከፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶችና ከክልሎች በሚቀርብ ጥያቄ 300 ሙያተኞችን ለማሰልጠን ታቅዶ 182 በመሰልጠናቸው አፈፃጸም 61% ነወ፡፡
- ☛ በሪከርድ ሥራ አመራር፣ በመዛግብት አስተዳደር እና በቤተመጻሕፍት ለ20 ሙያተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 19 በመሰልጠናቸው አፈጻጸም 95% ነው፡፡
- ☛ ከኤጅንሲው ውጪ ለሌሎች ተቋማት 108 የምክር አገልግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ 99 የምክር

  አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን አፈጸፀም 92% ነወ፡፡
- ✍ በስፖርት ዘርፍ በፌዴራል ደረጃ፣ በስፖርት ስልጠና ማዕከላት እንዲሁም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፣በስፖርት ማህበራቶች ጭምር የ1,950 የአስፈፃሚ አካላት አመራሮችን እና ባለሙያዎችን አቅም ለመገንባት ታቅዶ 1,341 አመራሮችና ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ዕቅዱን 68.8% ማከናወን ተችሏል፣

**ግብ 21፡ የዘርፍን ተቋም ግንባታ ማላቅ**

**<u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

- ✍ በዘርፉ 5 ልዩልዩ የአሰራር ማዕቀፎችን (የሕግ ማዕቀፎች፣ ስታንዳርዶች፣ ማኑዋሎች....ወዘተ) ለማዘጋጀት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ 6 ወራት 2 ስታንዳርዶችን ማለትም በትምህርት ተቋማት መኖር ስለሚገቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እና የስፖርት ውድድር ስታንዳርድ በማዘጋጀት የዕቅዱን 40% ማከናወን ተችሏል፣
- ✍ በሌላ በኩል ቀደም ሲል የተዘጋጁና ፀድቀው ስራ ላይ የሚውሉ 7 የህግ ማዕቀፎችንና ስታንዳርዶችን በማጠናቀቅ የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት በተያዘው ዕቅድ መሰረት፡-
  - ☞ የስፖርት ፖሊሲ/ ክለሳ፣
  - ☞ ረቂቅ የስፖርት አዋጅ/ኮድ/ህግ ዝግጅት፣
  - ☞ የሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን የተሻሻለ መመሪያ፣

- የስፖርት ማህበራት የውጤት አመልካችና መመዘኛ ሰነድ፣
- የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች የአስተዳደር፣ የአጠቃቀም እና የአጠባበቅ ማንዋል
- የስፖርት ልማት ፈንድ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ከተዘጋጁት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ለባለድርሻ አካላት ቀርበው ግብዓት እንዲሠጥባቸው በማድረግ የተወሰኑት ወደስራ የገቡ ሲሆን ሌሎቹን በሚመለከታቸው አካላት አፀድቆ ወደስራ የማስገባት ሒደት ላይ ይገኛሉ፡፡

## የትኩረት መስክ 6: ማህበረሰብ ትስስር፤ተጠቃሚነትና አጋርነት ማሳደግ

**ግብ 22፡ ቅንጅት፤አጋርነትና ዲፕሎማሲን በማጎልበት የአራቱን ተዋናዮች ሚና በዘርፍ ማላቅ**

## የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በብሔራዊ ቴአትር 41 የቅንጅትና ትብብር ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ 37 በማከናወን የእቅዱ 91% ተፈጽሟል፡፡ *ከስራዎቹም መካከል፡-*
- ከብሄራዊ የኪነጥበብ ስራዎች አስተባባሪ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን በወቅታዊና ሀገራዊ የሆኑ ላይ ጽሁፈ ተውኔቶችን የመገምገም ስራ ተካሂዷል፡፡
- ከኢትዮጵያ ቴአትር ባለሙያዎች ማህበር ጋር በመሆን ኢትዮጵያ ቴአትር የተጀመረበትን 100ኛ አመት አስመልክቶ በተካሄደ ፌስቲቫል ላይ በቅንጅት ተሰርቷል
- ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር የኪነጥበብ ማህበረሰቡ አጋርነቱን የሚገልጽበትን ስራዎች ለመስራት የተደረገ ስምምነት፡፡
- ከልደታ ክ/ከተማ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና ከእድገት በህብረት ት/ቤት ጋር በጋራ የተሰሩ ስራዎች፡፡
- ከሴቶች ጉዳይ ጋር ለመከላከያ ስንቅ ማዘጋጀት፣ነጩ ፖስታ፣ ችግኝ ተከላ ፤የኪነጥበብ ስልጠና ከባህልና ቱሪዝም ፤ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ እና ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን የባህልና ጥናትና ምርምር ጋር በመሆን
- ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በጋራ በስፖርት ኢንቨስትመንት የብቃት ማረጋገጫ እየተሰጠባቸው ያሉት መደቦችና ለወደፊቱ በስፖርት ኢንቨስትመንትና

ንግድ ስራ ሊሰጡ ይገባቸዋል ተብለው የታሰቡት ስራዎች መለየት እና ማሳወቅ ተችሏል

- ☞ 5 ባለሃብቶች በስፖርት ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፣
- ☞ የስፖርት ንግድ ኢንቨስትመንትና ማበረታቻዎች (incentives) ድራፍት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ ተዘጋጅታል፣
- ☞ የስፖርት ኢንቨስትመንትና ንግድ ስራ መስኮች እና የስራ እድል ፈጠራ ድራፍት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ ተዘጋጅታል፣

***ግብ 23፡ በዘርፍ የሚፈጠረዉን ገቢና የስራ እድል ማሳደግ፣***

## <u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- ☞ በባህል ዘርፍ ለ76,840 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 18,226 ዜጎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙ 18 በመቶ ደርሷል፣
- ☞ በባህል ዘርፍ 3800500 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 3450058 ብር በማሠባሰብ ዕቅዱን 90% ማከናወን ተችሏል፣
- ☞ በስፖርት ዘርፍ ለ3594 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ4,550 ዜጎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙ 100 በመቶ ደርሷል፡፡
- ☞ በስፖርት ልማት ዘርፍ 246,500,000 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ በብሄራዊ ፌዴሬሽኖች 35,348,447 ብር እንዲሁም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 197,397,315 ብር በድምሩ 232,745,762 ብር በማሠባሰብ ዕቅዱን 94.4% ማከናወን ተችሏል፣
- ☞ በባህል እና ስፖርት ዘርፍ በአጠቃላይ 250,300,500 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 236,195,820 ብር በማሰባሰብ ከእቅዱ 94% ማከናወን ተችላል፡፡

***ግብ 24፡ የዘርፉን የኮሙዩኒኬሽን እና ገፅታ ግንባታ ተግባራት አፈፃፀም ማሻሻል***

## <u>የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- ✍ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በውህደት መቋቋሙን ተከትሎ የተቋሞቹን ድህረ-ገፅ እና የማህበራዊ ገፆች (የፌስ ቡክ ገፅ፣ ቴሌግራም ቻናል እና የዩቲዩብ ቻናል) ወደ አንድ ማዋሃድ እና የስም ማስተካከያ ማድረግ

- የስፖርት ማህበረሰብ እና ሰራተኞች ለሃገር መከላከያ ሰራዊት የተደረገ ድጋፍ፣ የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር፣ የሚኒስትሮች የስራ ጉብኝት፣ በቶክዮ ኦሎምፒክ ዙሪያ፣ በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖሩ አርቲስቶች የቤት እድሳት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሴክተር ጉባኤ፣ የኪነጥበብ ባለሙዎች፣ የቻይና ኤምባሲ ቁሳቁስ ድጋፍ፣ ኢሬቻና ኦሮሚያን ይጎብኙና ሌሎች ሁነቶች መሰረት ያደረጉ ዜናዎችና የህትመት ውጤቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ተደርገዋል፣
- የስፖርት ዘርፍ ወቅታዊ መረጃዎች (የተዘጋጁ መልዕክቶች፣ መግለጫዎች፣ ዜናዎች፣ ቃለ-ምልልሶችና በመስክ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች) በየቀኑ በተቋሙ ሶሻል ሚዲያ እና በስፖርት ፖርታል ላይ እየተጫነ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ተደርገዋል፣
- 1 የሁነት ካላንደር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 1 የሚኒስቴሩ የስፖርት ውድድርና የኩነት ካላንደር ማዘጋጀት ተችሏል፣

### ግብ 25፡ የዘርፉን ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ የወጣቶች እና ሴቶች ተሳትፎ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ

- ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ለሚገኝ ሠራተኞች 100% እንክብካቤና የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት በመከናወኑ አፈፃጸም 100%ሆኗል፡፡
- 20,000, ችግኞች እንዲተከሉ እና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፣
- በዘርፉ 123,570 ሴቶችና ወጣቶችን በበጀት ዓመቱ 6 ወራት ተሳታፊ እና በስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በስፖርት ዘርፍ 78,500 ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በማድረግ የዕቅዱን 63.5% ማካት ተችሏል፣

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | ግብ1 የብ/ብ/ህዝቦች የቋንቋዎች አጠቃቀምን ማጎልበት | | የስነቃል የስልጠና ማኑዋል ረቂቅን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100% |
| | | | የኩሱሜ ቋንቋን የመጀመሪያውን ረቂቅ በብሄረሰቡ አባላት በማስተቸትና በማረም ለህትመት ተዘጋጅቷል፡፡ | | 1 | 1 ረቂቅ | 1 | 100% |
| | ግብ 2፡ የብሄር ብሄረሰቦች የስነ- ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማጎልበት | በቁጥር | በቴአትር ቤቱ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ የቴአትር ትርዒቶችን ለሕዝብ ማቅረብ | 99 | 387 | 155 | 156 | 100% |
| | | በቁጥር | ልዩ ልዩ የሙዚቃ ትርዒቶችን በማእከል በክልልና በውጭ ሀገራት ለሕዝብ ማቅረብ | 40 | 182 | 82 | 50 | 61% |
| | | በቁጥር | በኪነጥበብ ኢንተርፕራይዞች፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች የሚቀርቡ የአዳራሽ ዝግጅቶችን ማስተናገድ | 130 | 158 | 71 | 149 | 100% |
| | | በቁጥር | በግል የኪነ-ጥበብ ቡድኖች ተዘጋጅተዉ የተስተናገዱ መደበኛ ትርኢቶች በቁጥር | 44 | 82 | 37 | 102 | 100%+ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር | የኪነጥበብ አገልግሎት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች | 8,183,587 | 6,648,568 | 250,000 | 261,666 | 100 |
| | | በቁጥር | የተዘጋጁ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ትውፊታዊ ትውን ጥበባት ዜማዎች | 8 | 7 | 3 | 2 | 75 |
| | | በቁጥር | ልማታዊ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው በመድረክ ፣ሬድዮና ቴሌቪዥን የቀረቡ ቴአትር ዝግጅቶች | 2 | 4 | 2 | 1 | 50 |
| | | በቁጥር | ልማታዊ ጉዳዮች ላይ በመገናኛ ብዙሀን የቀረቡ ዘመናዊና ባህላዊ ሙዚቃ ህብረዝማሬዎች / ዜማዎች ዝግጅቶች | 12 | 13 | 4 | 7 | 100 |
| | | በቁጥር | የኪነ-ጥበብ ዘርፉ ለሀገር ልማትና ለማህበረሰብ ግንባታ የተዘጋጁ ሀገር አቀፍ የንቅናቄ መድረኮች | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጁ አዳዲስ የሙዚቃና የቴአትር ጥበብ ሥራዎች ብዛት | 10 | 30 | 10 | 12 | 100 |
| | | በቁጥር | አዳዲስ የተዘጋጁ የሙዚቃ ጥበብ ሥራዎች ብዛት | 9 | 28 | 9 | 11 | 100 |
| | | በቁጥር | አዳዲስ የተዘጋጁ የቴአትር ጥበብ ሥራዎች ብዛት | 1 | 2 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | ለምዘና የቀረቡ የቴአትርና የሙዚቃዊ ቴአትር ድርሰቶችና ፕሮዳክሽኖች በቁጥር፣ | 7 | 13 | 5 | 11 | 100 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር፣ | ተሰብስበው ለምዘና የቀረቡ የዘመናዊና የባህል ሙዚቃ ግጥሞች ዜማዎችና ቅንብሮችበቁጥር፣ | 10 | 52 | 20 | 25 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | የተሠሩ የማስታወቂያ ሥራዎች ዓይነት በቁጥር፣ | 8 | 9 | 6 | 16 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | የተሰራጩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች በቁጥር፣ | 194 | 730 | 297 | 76 | 26 |
| | | በቁጥር፣ | የተሰራጩ የማስታወቂያ ፖስተሮች፣ ሊፍሌቶችና ፍላየሮች በቁጥር፣ | 3500 | 30450 | 12150 | 63 | o.5 |
| | | በቁጥር፣ | በቴአትር ሙያዎች በማዕከልና በክልል ለሚገኙ ለወጣትና ጀማሪ ኪነጥበብ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት | 168 | 128 | 52 | 120 | 63 |
| | | በቁጥር፣ | በቴአትር ሞያ የቴክኒክ መርጃ ጽሁፍ ማሰራጨት | 1459 | 2000 | 700 | 665 | 63 |
| | | በቁጥር፣ | በሙዚቃ ሞያ የቴክኒክ መርጃ ጽሁፍ ማሰራጨት | 200 | 200 | 120 | 114 | 95 |
| | | በቁጥር | አዲስ የተሠበሰቡ የመረጃ ሀብቶች ክምችት በቁጥር | 30 | 105 | 45 | 45 | 100 |
| | | በቁጥር | የተደራጁ የመረጃ ሀብቶች በቁጥር | 30 | 105 | 45 | 45 | 100 |
| | ግብ 3: የዕደ-ጥበብ ምርትን ማሰፋፋትና ገበያን ማጎልበት | የአቅም ግንባታ እና | በሁለት (2) ክልሎች ሞዴል ማምረቻ እና መሸጫ የሚሆኑ ማዕከላት እንዲደራጁ የአቅም ግንባታ እና የክህሎት ስልጠና | 6 | 5 | - | - | - |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | የክህሎት በቁጥር | መስጠት፣ ድጋፍ ማድረግና መከታተል፣ | | | | | |
| | | በቁጥር | ለባህል ምርቶች  መለያ (ብራንድ) ሰነድ ማዘጋጀት | | 2 | 2 | 2 | 100 |
| | | በቁጥር | የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ለማድረግ መለየት | - | 5 | 2 | 1 | 50 |
| | ግብ 4: የዕይታዊ፣ ትዕይንታዊ እና ሰነ-ፅሁፍ ጥበባት ኢንዱስትሪን በማጎልበት የጨዋ ገበያ ተደራሽ ማድረግ፣ | በቁጥር | በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተግባራዊ የተደረገ ማበረታቻ ስርዓት (ዓመታዊ የሽልማትና እውቅና ፕሮግራም) በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 0.4 | 40 |
| | | በቁጥር | ለፊልም ፖሊሲ ማስፈፀሚያ የተዘጋጀ ሕግ ማእቀፍና ስትራቴጂ - በቁጥር | 0.5 | 1 | 0.9 | 0.7 | 77 |
| | | በቁጥር | የተሻሻሉ የባህል ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ስትራቴጂዎች እና አሰራር ስርአት ሰነዶች ዝግጅት | 5 | 6 | 100 | 25 | 25 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር | የህዝቦችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠናክር ሙዚቃዊ ትርኢት (ድንቅነሽ ኢትዮጵያ) መድረኮች ማካሔድ | - | 100 | 100 | 10 | 35 |
| | | በቁጥር | ከሙያ ማህበራት ጋር በዕቅድ እና ልዩ ልዩ አፈፃፀም የተደረጉ ምክክሮች | 1 | 100 | 100 | 25 | 50 |
| | ግብ 6: አገር በቀል እውቀቶችን በመጠበቅ ማልማት | በቁጥር | በየአካባቢዉ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ ለመፍታት ያደገ አቅም/ከሀገር ሽማግሌዎች፣ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶች ማድረግ/ | 2 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| | | በቁጥር | የአለማቀፍ የመቻቻል ቀንን ማክበር | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | መስቀል በአል የውይይት መድረክ ማዘጋጀት | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | በተደራጁ የንባብ ክበባት አገልገሎት መስጠት | 2811100 | 1157000 | 1230000 | 1169000 | 95 |
| | | በቁጥር | በሚካሄዱ የንባብ ሳምንታት አገልግሎት መስጠት | 69750 | 2000 | 50000 | 0 | 0 |
| | | በቁጥር | የንባብ አገልግሎት ህብረተሰብ ክፍል የህብረተሰብ | 9969399 | 7977700 | 1967322 | 1742235 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር | ከህዝብ ክንፍ ፣ ከክልሎች ከከተማ መስተዳድር ጋር በመቀናጀት የተካሄዱ ሴሚናሮች (ብሔራዊ እና የህዝብ ቤተመጽሐፍት የባህል ንግግር(Cultural dialog) ለማዳበር የተዘጋጁ አውደጥናቶች) | 6 | 4 | 2 | 2 | 100 |
| | | በቁጥር | ከህዝብ ክንፍ ፣ ከክልሎች ከከተማ መስተዳድርና ከባለድርሻአካላት ጋር በመቀናጀት ፐብሊክ ሌክቸር ማካሄድ | 8 | 9 | 5 | 4 | 80 |
| | | በቁጥር | ከህዝብ ክንፍ ፣ ከክልሎች ከከተማ መስተዳድርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አውደ ርዕይ ማዘጋጀት (በጥያቄ) | 4 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | ከህዝብ ክንፍ ፣ ከክልሎች ከከተማ መስተዳድርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አውትሪቺንግ ማካሄድ | 9 | 6 | 3 | 5 | 167 |
| | | ቁጥር | የንባብ ባህልን ለማስፋፋት የተደረገ የንቅናቄ ፕሮግራሞችን | 11 | 7 | 7 | 6 | 85 |
| | | በቁጥር | የህጻናት የንባብ ባህል ለማሳደግ ንቅናቄ ማቀጣጠያ የንባብ ሳንምታት በጋራ መኖሪያ ቤቶች ማዘጋጀት | 1 | 4 | 3 | 2 | 67 |
| | | በቁጥር | የንባብ ክበባት ማደራጀት | 101 | 80 | 40 | 10 | 25 |
| | | በፐርሰንት | የንባብ ባህል ሽፋንን ማሳደግ | 18.5 | 36 | 21 | 18.5 | 88 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር | የመረጃ ሀብቶችን በማሰባሰብ ክምችት ማሳደግ | 105410 | 142180 | 43779 | 40841 | 93 |
| | | በቁጥር | የመረጃ ሀብቶችን ማደራጀት | 94170 | 61362 | 38499 | 41056 | 100 |
| | | በቁጥር | ለመረጃ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ | 82960 | 82990 | 14555 | 18235 | 100 |
| | | በቁጥር | መዛግብት ሊያዛውሩ ከሚችሉ የፌደራል የመንግስት መ/ቤቶች ጋር በሪከርድ ምዘናና መረጣ በጋራ መስራት | 5 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | የውዝፍ ሪከርዶች ምዝገባ፣ የምዘናና መረጣ እና የመለያ ቁጥር መስጠት ሥራ ማከናወን | 2488 | 955 | 600 | 483 | 81 |
| | | በቁጥር | ለህዝብ ቤተመጽሐፍት መጽሐፍት ማሰራጨት | 56780 | 25631 | 18150 | 19228 | 106 |
| | | በቁጥር | በክልል ከተሞች ለተቋቋሙ አብያተ መዛግብትና ቤተመጽሐፍት ማዕከላት የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ መስጠት | 13 | 8 | 5 | 3 | 60 |
| | | በቁጥር | የጽሑፍ ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ድስክርብሽን ማዘጋጀትና መላክ | 2 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| | | በቁጥር | 12ቱን የፅሁፍ ቅርሶች በአገር ውስጥ ቱሪሰቶች ማስጎብኘት | 2431 | 1872 | 900 | 986 | 110 |
| | | በቁጥር | 12ቱን የፅሁፍ ቅርሶች በ ውጪ አገር ቱሪሰቶች ማስጎብኘት | 208 | 76 | 30 | 35 | 117 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | በኤጀንሲው ዕቅድ አፈፃጸምና በፕሪግራም በጀት ላይ ክትትል በማድረግ ድጋፍ መስጠት | 24 | 24 | 6 | 6 | 100 |
| | ግብ 10፡ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ ማዘመንና ማሻሻል | | የዓላማ አስፈጻሚ አ/ት አውቶሜሽን ሶፍትዌር በዋረንቲ ጊዜ የሚስተካከሉ እና በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መከታተልና በአልሚው ድርጅት እንዲፈቱ ማድረግ | - | 3 | 3 | 3 | 100 |
| | | | የኤጀንሲውን ፖርታል የኦንላይን አገልግሎቶችን አካቶ ማልለማት | - | 2 | 1 | 1 | 100 |
| | | | በኤጀንሲው ለለማው ሶፍትዌር ለኦንላይን አገልግሎት ለማዘጋጀት የዲጂታይዜሽን ሥራዎችን ማስጀመር | - | 2 | 2 | 0.5 | 25 |
| | ግብ 11 የህዝባዊ እና መንግስታዊ ስፖርት አደረጃጀቶችን በመፈተሽ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ | | የተደራጁ መንግስታዊ የስፖርት ተቋማት ብዛት፣ | 1,261 | 1,321 | 1,321 | 1,261 | 95 |
| | | | የተደራጁ ሕዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች ብዛት፣ | 122,904 | 134,449 | 128,676 | 122,904 | 95 |
| | | | የተደረጉ የስፖርት ም/ቤቶች/ ተቋም ብዛት | 10,950 | 15,720 | 15,720 | 7,431 | 47 |
| | | | ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አስፈፃሚ እና የሚሚያ ምርጫ ያካሄዱ ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ብዛት | 28 | 31 | 31 | 26 | 84 |
| | | | ስታንዳርዱን አሟልተው የተደረጁ ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ብዛት፣ | 4 | 6 | 4 | 3 | 75 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | ኦዲት የተደረጉ ሕዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች ብዛት፣ | 1,308 | 1,504 | 1,504 | 820 | 54 |
| | ግብ 12 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በማሳደግ ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥና ተደራሽ ማድረግ፣ | | | | | | | |
| | | | በግል የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | 2 | 5 | 3 | | 33 |
| | | | ወደመረጃ ቋት የገቡ በትምህርት ቤቶችና እና በተቋማት ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | 27,542 | 41,256 | 38,688 | 30,700 | 79 |
| | | | ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ያላቸው የማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | 36,122 | 41,256 | 38,688 | 30,700 | 79. |
| | | | ሀገር አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | 73 | 142 | 107 | 78 | 72 |
| | | | የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተደራሽነት በመቶኛ፣ | 16 | 17 | 17 | 16 | 94 |
| | | | በመስሪያ ቤቶች በጤናና በአካል ብቃት ተሳታፊ ብዛት፣ | 239,576 | 300,000 | 300,000 | 421,023 | 100 |
| | | | በጤና ቡድኖች በጤናና በአካል ብቃት ተሳታፊ ብዛት፣ | 190,000 | 200,000 | 200,000 | 546,586 | 100 |
| | | | ደንቦች እና የጨዋታ ህጎች ወጥቶላቸው የተስፋፉ የባህል ስፖርቶች ብዛት፣ | 10 | 11 | 1 | 50.0% | 50 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | በየደረጃው የተዘጋጁ የባህል ስፖርት ፌስቲቫሎች ብዛት፣ | 1,252 | 1,452 | 400 | 163 | 40 |
| | | | በስፖርታዊ ፌስቲቫሎች የተሳተፈ የሕብረተሰብ ብዛት፣ | 10,424,111 | 12,000,000 | 6,000,000 | 3,956,311 | 66 |
| | | | የብሄራዊ ስታዲየም ምዕራፍ 2 ግንባታ ዙሪያ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ቀናቶች ብዛት፣ | 365 | 365 | 180 | 180 | 100 |
| | | | ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸውነባርና አዲስ አገልግሎት የሚሠጡ የማሰልጠኛ ማዕከላት ብዛት፣ | 16 | 19 | 19 | 16 | 84 |
| | | | ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው በግንባታ ላይ የሚገኙ የማሰልጠኛ ማዕከላት ብዛት፣ | 12 | 12 | 12 | 12 | 100 |
| | ግብ 13 በየደረጃው የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትን በማስፋፋት የሚሳተፈውን ህብረተሰብና የተሳትፎ ሽፋኑን ማሳደግ፤ | | የህብረተሰቡ በጤናና አካል ብቃት ተሳትፎ በመቶኛ፣ | 19% | 20% | 20% | 18.20% | 91 |
| | | | በት/ቤቶች በጤናና በአካል ብቃት ተሳታፊ ብዛት፣ | 20,932,033 | 23,575,000 | 23,575,000 | 18,160,00 | 77 |
| | | | በመስሪያ ቤቶች በጤናና በአካል ብቃት ተሳታፊ ብዛት፣ | 239,576 | 300,000 | 300,000 | 421,023 | 100 |
| | | | በጤና ቡድኖች በጤናና በአካል ብቃት ተሳታፊ ብዛት፣ | 190,000 | 200,000 | 200,000 | 546,586 | 100 |
| | | | ደንቦች እና የጨዋታ ህጎች ወጥቶላቸው የተስፋፉ የባህል ስፖርቶች ብዛት፣ | 10 | 11 | 1 | 50 | 50 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | በየደረጃው የተዘጋጁ የባህል ስፖርት ፌስቲቫሎች ብዛት፣ | 1,252 | 1,452 | 400 | 163 | 40 |
| | | | በስፖርታዊ ፌስቲቫሎች የተሳተፈ የሕብረተሰብ ብዛት፣ | 10,424,111 | 12,000,000 | 6,000,000 | 3,956,311 | 66 |
| | | | በስፖርት ኩነቶች የተሳተፈ ህብረተሰብ ብዛት፣ | 13,255,138 | 14,000,000 | 7,000,000 | 4,913,247 | 56 |
| | ግብ 14 የኤሊት (የአዋቂ እና የላቁ) ስፖርተኞችን ቁጥርን ማሳደግ | | በዋና ክለብ ላይ በተከታታይነት መሳተፍ የቻሉ ኤሊቶች ብዛት | 490 | 628 | 628 | 186 | 29. |
| | | | በአዋቂ ብሄራዊ ቡድን የተሳተፉ ኤሊቶች ብዛት | 200 | 330 | 100 | 57 | 57 |
| | | | በአለም አቀፍ ደረጃ የተሳተፉ እና ውጤታማ የሆኑ ኤሊቶች ብዛት | 60 | 90 | 30 | 43 | 100 |
| | ግብ 15 በአህጉርና አለም አቀፍ ደረጃ በልዩ ልዩ የስፖርት አይነቶች በመሳተፍ ውጤት | | ተሳትፎ የተደረገባቸው የስፖርት አይነቶች ብዛት | 11 | 17 | 11 | 9 | 81 |
| | | | በቶኪዮ ኦሎምፒክ | - | 6 | 6 | 4 | 66 |
| | | | ውጤት የተመዘገበባቸ የስፖርት አይነቶች ብዛት | 7 | 11 | 4 | 5 | 100 |
| | ግብ 16 የተዘጋጁ ሀገር አቀፍ የውድድር መድረኮችን ማሳደግ | | ክልል አቀፍ/ከተማ አቀፍ የውድድር መድረኮች ብዛት | 118 | 197 | 197 | 99 | 50 |
| | | | በክልል/ከተማ አቀፍ ደረጃ ውድድር የተዘጋጀባቸው የስፖርት ዓይነቶች ብዛት፣ | 15 | 25 | 25 | 13 | 52 |
| | | | በክልል ከተማ አቀፍ መድረኮች የተሳተፉ አትሌቶች ብዛት | 28,250 | 45,866 | 45,866 | 32,775 | 71 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | ሀገር አቀፍ የውድድር መድረኮች ብዛት፣ | 68 | 118 | 118 | 78 | 66 |
| | | | ውድድር የተካሄደባቸው ስፖርቶች ብዛት፣ | 20 | 29 | 29 | 7 | 24 |
| | | | በሀገር አቀፍ ውድድሮች የተሳተፉ አትሌቶች ብዛት፣ | 14,437 | 28,000 | 28,000 | 12,000 | 43 |
| | | | ስታንዳርድን የጠበቀ የውድድር የሚመሩ ፌዴሬሽኖች ብዛት፣ | 4 | 5 | 4 | 5 | 80 |
| | ግብ 17.የስፖርት ማህበራዊ ልማትና ዲፕሎማሲን ማሳደግ፣ | | ስፖርትን ለማህበራዊ ልማት የሚጠቀሙ ተቋማት ብዛት፣ | 20 | 34 | 34 | 24 | 71 |
| | | | በስፖርት ማህበራዊ ልማት የተሰማሩ የሲቪክ ማህበራት ብዛት፣ | 12 | 20 | 20 | 14 | 70 |
| | | | በስፖርት ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞች ብዛት፣ | 3,750 | 10,000 | 5,000 | 3,500 | 70 |
| | | | በስፖርት ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ብዛት፣ | 32,900 | 100,000 | 50,000 | 32,100 | 64 |
| | | | በስፖርት በጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሰማራ ህብረተሰብ ብዛት፣ | 9,907 | 10,392 | 5,196 | 4,370 | 84 |
| | ግብ18፡ የዘርፉን ማኅልበት/የመረጃ አሰባሰብ አያያዝ አጠቃቀምና መረጃና የመረጃ ቴክኖሎጂ | | በቴአትር ቤቱ ዌብሳይት /ድረ-ገጽ / የተጨመሩ አዳዲስ መረጃዎች በቁጥር፣ | 74 | 77 | 40 | 48 | 100 |
| | ግብ 19፡ የዘርፉን የጥናትና ምርምር ሥራዎችን | | የዳሰሳ ጥናቶች ማካሄድ | 14 | 15 | 4 | 3.92 | 98 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | በብሔራዊ ቴአትር የተሰሩ ጥናትና ምርምሮች | | 4 | 2 | 2 | 100 |
| | | | የተከናወኑ ልዩ ልዩ ደረጃ ያላቸው የጥናት እና ምርምር ስራዎች፤ | 30 | 28 | 8 | 10 | 100 |
| | ግብ 20፡ የዘርፉን የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማጎልበት | በመቶኛ | ቴአትር ቤቱ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች የተሳተፉና ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች በመቶኛ | 50 | 67 | 60 | 50 | 83 |
| | | | በባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ ሙያዎች በማዕከልና በክልል ለሚገኙ ለወጣትና ጀማሪ ኪነጥበብ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት | 196 | 332 | 128 | 100 | 63 |
| | | | በሪከርድ ሥራ አመራር በመዛግብት አስተዳደር እና በቤተመጻሕፍት፣ሙያዎች ላይ መደበኛ መርሀግብር ሙያተኞች ማሰልጠን | 798 | 920 | 165 | 151 | 92 |
| | | | በሪከርድ ሥራ አመራር በመዛግብት አስተዳደር እና በቤተመጻሕፍት፣ ሙያዎች ላይ በሚቀርብ በጥያቄ መርሃ ግብር ስልጠና መስጠት | 932 | 520 | 300 | 182 | 61 |
| | | | በሪከርድ ሥራ አመራር በመዛግብት አስተዳደር እና በቤተመጻሕፍት፣ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | 19 | 25 | 20 | 19 | 95 |
| | | | በስፖርት ዘርፍ አቅማቸው የተገነባ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ | 1,909 | 2,601 | 1,950 | 1,341 | 69 |
| | | | በስፖርት ዘርፍ የአጫጭር ጊዜ ስልጠና የወሰዱ የስፖርት ባለሙያዎች ብዛት፣ | 7,154 | 6,500 | 3,500 | 2,606 | 75 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | | የመካከለኛ ጊዜ ስልጠና የወሰዱ የስፖርት ባለሙያዎች ብዛት፣ | 264 | 280 | 150 | 78 | 52 |
| | | | የረዥም ጊዜ ትምህርት የወሰዱ የስፖርት ባለሙያዎች ብዛት፣ | 41 | 30 | 30 | 11 | 37 |
| | | | የሙያ ብቃት ማረጋገጫ /COC የወሰዱ የስፖርት ባለሙያዎች፣ | 40 | 900 | 300 | 500 | 100 |
| | ግብ 21. የዘርፍን ተቋም ግንባታ ማላቅ | | ለድሬዳዋ፣ ለጋምቤላና ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የቋንቋ፣ሥነቃልና ትርጉም ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና በመስጠት አቅም መገንባት ተችሏል፡፡ አፋር ክልል በጸጥታ ችግር አለተሳተፈም፡፡ | 22 | 26 | 2 | 75 | 75 |
| | | | ለሚዲያ አካላት እና ለአስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ | | 2 | 1 | 1 | 100 |
| | | | የተዘጋጁ ልዩ ልዩ የአሰራር ማዕቀፍች፣ | 8 | 15 | 5 | 2 | 40 |
| | ግብ 22፡ ቅንጅት፣አጋርነትና ዲፕሎማሲን በማጎልበት የአራቱን ተዋናዮች ሚና በዘርፍ ማላቅ | በቁጥር፣ | በቅንጅትና ትብብር የተሰሩ ስራዎች በቁጥር | 43 | 86 | 41 | 37 | 90 |
| | | በቁጥር፣ | በቴአትር ጥበብ በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 5 | 12 | 6 | 6 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | በሙዚቃ ጥበብ በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 7 | 34 | 16 | 9 | 95 |
| | | በቁጥር፣ | በጥናትና ስልጠና በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 2 | 8 | 3 | 3 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | በአዳራሽ ትብብር በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 23 | 22 | 10 | 14 | 100 |
| | | በቁጥር፣ | በሕዝብ ግንኙነት በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 4 | 7 | 4 | 3 | 75 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጅክ ግብ | መለኪያ | አመላካች | የ2013 አፈጻፀም | የ2014 ዒላማ | የ6 ወር እቅድ አፈፃፀም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዒላማ | አፈጻጸም | በ% |
| | | በቁጥር፤ | በወጣቶችና ሴቶች በቅንጅትና ትብብር መሥራት | 2 | 3 | 2 | 2 | 100 |
| | | በቁጥር፤ | በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ትርዒቶች ብዛት በቁጥር | 2 | 4 | 2 | 1 | 50 |
| | ግብ 25፡ የዘርፉን ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ የወጣቶች እና ሴቶች ተሳትፎ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ | | በሚሰጡ አገልግሎቶች ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ | 937153 | | 349000 | 318000 | 91 |
| | | | በሚሰጡ አገልግሎቶች ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ | 1574888 | | 423000 | 393000 | 93 |
| | | | በሚሰጡ አገልግሎቶች ህጻናትን ተጠቃሚ ማድረግ | 19200 | | 12000 | 6897 | 57 |
| | | | በሚሰጡ አገልግሎቶች ማየት የተሳናቸውን ተጠቃሚ | | | 300 | 140 | 47 |
| | | | በኤች አይ ቪ ኤድስ ለተጎዱ ወገኖች የገንዘብ ድጋፍ | 100 | | 100 | 100 | 100 |

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት የገቢ ዕቅድ አፈጻጸም ሠንጠረዥ

| ተቋም | የገቢ አይነት | የ2014 የገቢ ዕቅድ | የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% | |
| ዋናው መስሪያ ቤት | ከአዲስ አበባ ስታዲየም ዙሪያ ቤቶች ኪራይ ገቢ | 5,000,000 | 1,250,000 | 1,250,000 | 100 | |
| የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | ከቴአትር ትርዒት፣ከሙዚቃ ትርዒትና ከአዳራሽ አገልግሎት የተገኘ ገቢ | 8,219,500 | 3,692,500 | 3,397,598 | 92 | |
| ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት | ለተገልጋዮች ከሚሰጡ የውስጥ አገልግሎቶች | 231,000 | 108,000 | 62,460 | 76 | |
| | | **13,450,500** | **5,050,500** | **4,710,058** | **93** | |

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት **የመደበኛ ወጪ** አፈጻጸም ሡንጠረዥ

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የወጪ አይነት | ለ2014 የተፈቀደ በጀት | የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | **እቅድ** | **ክንውን** | **አፈጻጸም** | |
| 1 | ዋናው መ/ቤት | መደበኛ | 282,585,200 | 123,514,156 | 55,954,064 | 45 | |
| 2 | ቤት መዛግብትና ቤት መጻሕፍት | መደበኛ | 81,145,702 | 29,993,680 | 22,527,201 | 76.6 | |
| 3 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | መደበኛ | 56,728,030 | 27186712 | 12058994 | 44.4 | |
| 4 | የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | መደበኛ | 73,102,400 | 37,080,125 | 25,846,237 | 69.7% | |
| 5 | የአትሌት ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል | መደበኛ | 61,841,415 | 38,606,784 | 30,308,393 | 78.5% | |
| 6 | የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን | መደበኛ | 23,383,780 | 9,140,535 | 12,432,379 | 100% | |
| | **ድምር** | | **578,786,527** | **265,521,992** | **159,127,268** | **62%** | |

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት <u>የካፒታል ወጪ</u> አፈጻጸም ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የወጪ አይነት | ለ2014 የጸደቀ በጀት | የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻተም | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | እቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | |
| 1 | ዋናው መ/ቤት | ካፒታል | 2,537,976,200 | 984,857,742 | 105,507,101 | 10 | |
| 2 | ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት | ካፒታል | 147,000,000 | 146,430,000 | 83,707,549 | 57 | |
| 3 | የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | ካፒታል | 21,265,000 | 13,800,000 | 9,795,044 | 71 | |
| ድምር | | | **2,706,241,200** | **1,145,087,742** | **199,009,694** | 17 | |

## 5) የተቋሙ የኦዲት ግኝት ምልከታ

ባለፉት ዓመታት የፋይናንስ አጠቃቀም ስርዓቱ በዉስጥ ኦዲተርና በዋና ኦዲተር የሂሳብ አያይዝና እና ግምጋማ ቀድሞ በነበረው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሁም ስፖርት ኮሚሽን የተፈቀደ የስፖርት ልማት ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች የኦዲት ግኝት ደረጀዎች ምርመራ (Except for) ነው፡፡

የውስጥ አዲት ግኝት ሪፖርት የሚዘጋጀው በየሩብ ዓመቱ ሲሆን ራፖርቱም በግልባጭ ለገንዘብ ሚኒስተር የሚላክ ሆኖ ለአመራሩ የፋይናንስ ሪፖርቶችን እንዲያዉቁት የሚደረግ ሲሆን አጠቃለይ የሂሳብ ሪፖርቱ እንደደረሳቸው ይደረጋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ግኝትም እንደዚሁ ለሚመለከታቸው ሁሉ የግኝት ውጤት ሪፖርት ያሳውቃል፡፡ የሪፖርት ምርመራው የሚያዘው የፋይናንስ እና የህገዊነት ኦዲት ምርመራ ዉጤትን በዚህ ውስጥ የተጣሰውን የፋይናስ አስተዳደር ህግ እና መንግስት ያወጣቸውን ደንብና መመሪያ ጭምር ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ ፕሮግራምና እና ፕሮጀክቶች የምርመራ ዉጤት ምርመራ አድርጎ ግብረመልስ የሰጠ ሲሆን በዚሁ መሰረት የተሰጠውን ጉድለቶች መነሻ በማድረግ የእርምትና የማስተካከያ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 6) ተቋማዊ ለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም

አዲስ የመንግስት ምስረታ ተከትሎ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ስፖርት ዘርፎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተባብር እና የሚከታተል ተቋም "የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር" በሚል ስያሜ እንዲቋቋም መደረጉ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴሩ በአዋጅ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን እንዲሁም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ኮሚቴ በማደራጀት አዲስ መዋቅር ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን መዋቅሩ የሰው ሃይል ትመናን ወጭ ቆጣቢ፣ ቢሮክራሲን ያሳጠረ፣ ፕሮፌሽናሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ፣ የተቋሙን ተገልጋዮች ያማከለ እና አገልግሎት አሰጣጥን ሊያሳልጥ በሚችል መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው መዋቅር በአመራር ደረጃ ተደጋጋሚ ውይይትና ማስተካከያዎችን በማድረግ ፀድቆ ወደተግባር እንዲገባ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

መላክ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ በሚኒስቴሩ ውጤትን መሠረት ያደረገ አመራርና ክትትልና ግምገማን ተግባራዊ በማድረግ የሚኒስቴሩን ተልዕኮ ለማሳካት ዝግጅት ማድረግ ተችሏል።

የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው መፈታት ያለባቸውን ችግሮች መለየት የተቻለ ሲሆን በየደረጃው ተዘጋጅተው የፀደቁ መመሪያዎችን፣ የአሠራር ሥርዓቶች እና ማኑዋሎችን (በዋናው መ/ቤት፣ በክልሎች፣ በአካዳሚዎችና በስፖርት ማህበራት) በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ መከታተል፣ የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በወቅቱ ያለመቅረብ /የግዥ መጓተት እና የጥራት ችግሮችን ለመፍታት በግገር ኮሚቴ የቅርብ ክትትል ማድረግ፣ የተበላሹና መጠገን የሚገባቸው ንብረቶች በፍጥነትና በተሟላ ሁኔታ በመጠገን ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ የታዳጊ ወጣቶች እንዲሁም የስፖርት ባለሙያዎች ስልጠና መረጃ አያያዝ ችግር እንዲፈታና ፍትሃዊ ያልሆኑ የስልጠና ስርዓቶችን እና የዕድሜ ማጭበርበር ለመቅረፍ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደተግባር ማስገባት፣ በብሄራዊ ስታዲየም ግንባታ የውጪ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ በከፍተኛ አመራሮች ጥረቶች መደረጋቸው፣ በየክልሉ የሚገነቡ ስታዲየሞች በተያዘላቸው መርሃ-ግብር መሠረት እንዲጠናቀቁ ሙያዊ ድጋፎች ማድረግ የተቻለ ሲሆን በቀጣይ እኚህና ሌሎች የመልካም አስተዳር ችግሮች እንዲፈቱ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

**አደረጃጀትን ተቋማዊ ማድረግ**

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በገንዘብ ሚኒስቴር አዲሱን የመንግስት አደረጃጀት መሰረት በማድረግ ከተዋሃዱ፣ ከተለያዩ እና አዲስ ከተፈጠሩ መ/ቤቶች የሚጠበቁ ተግባራት እና ኃላፊነቶች ምን መሆን እንዳለበት በላከው መመሪያ መሰረት መ/ቤታችን የተለያዩ ተግባራትን በሁለተኛው ሩብ አመት አከናውኗል፡፡

**የባህልና ስፖርት ዘርፍ በጀትን ስለማዋሃድ**

የባህል እና ስፖርት ዘርፎች በአንድ ሚኒስቴር ስር በመዋሀዳቸው ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላከ የአሰራር መመሪያን መሰረት በማድረግ ቀደም ሲል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን ይጠቀምበት የነበረው እና ለዉህደቱ የሚያስፈልጉ በጀት ከIFMIS የተገኙ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ለ2014 በጀት ዓመት በገንዘብ ሚኒስቴር የተፈቀደ በጀት፣ ከሐምሌ 1/2013 እስከ ታህሳስ 13/2014 ዓ.ም የተደረጉ የገቢና ወጪ ሪፖርቶች /Monthly Fiance Report በመመልከት፣ የበጀት አፈፃፀም ሪፖርት በማሰባሰብ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚገኙ ቀሪ ከስፖርት ኮሚሽን ወደ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የበጀት ዝዉዉር በመፈጸም፣ እንዲሁም በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስም የነበረው አካውንት እንዲዘጋ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አዲስ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

አካውንት በመክፈት ሂሳብ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ተችሏል። የተቋሙ ውህደት የሚያስፈልገውን የፕሮግራም፣ ዋና ተግባርና የፕሮጀክት በጀት በዝርዝር መርሃ-ግብር ተዘጋጅቷል።

**ክፍያና ሂሳብን በሚመለከት**

የ2013 በጀት ዓመት በጀትን በተናጠል በፌዴራል ዋና ኦዲተር ኦዲት በማስደረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ማሳወቅ ተችሏል። በመቀጠል ለ2014 በጀት ዓመት ከፀደቀዉ በጀት ውስጥ በመደበኛ እና ካፒታል በጀት ከሐምሌ1/2013 እስከ ህዳር 30/2014 ከገንዘብ ሚኒስቴር ትራንስፈር ሆኖ በባንክ (በZero B & D) አካዉንት ከወጪ ቀሪ ሂሳብ የማረጋገጥ፣ በስፖርት ኮሚሽን በIFMIS ሂሳብ መዝገብ የሚታየዉን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦች እስከ ታህሳስ 30/2014 ዓ.ም ድረስ ያለዉን በዉስጥ ኦዲት በማስመርመር በአዲሱ አደረጃጀት ወደ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሂሳብ መዝገብ 332 እንዲመዘገብ በማድረግ እንዲሁም በስፖርት ኮሚሽን ስም በብሔራዊ ባንክ የሚገኙ የእርዳታ ሂሳቦች ከወጪ ቀሪ ተለይቶ ወደ 332 የሂሳብ መዝገብ ወደ እርዳታ ሂሳብ D አካዉንት በኦዲት ተመርምሮ እንዲተላልና የታህሳስ 2014 ዓ.ም የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሰራተኞች መረጃ በማጠናቀር ደመወዝ እንዲከፈል ማድረግ ተችሏል። በአዲሱ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ስያሜ በተከፈተው የባንክ አካውንት ጊዜያዊ የፋይናስ ኃላፊ በመወከል እና የባንክ ውክልና በመስጠት አዲስ በተከፈተው አካውንት ሂሳብ ገቢና ወጪ እየተደረገ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በአዲሱ አደረጃጀት የቱሪዝም ልማት ፕሮግራምን ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በመነጠል የበጀት ዝዉዉር መፈፀም ተችሏል፡፡

**ንብረትን በሚመለከት**

በስፖርቱ ዘርፍና በባህሉ ዘርፍ በተናጥል ያሉ ንብረቶች የሚቆጥሩ፣ የሚለዩና የሚያዋህዱ ኮሚቴዎችን ማዋቀር የተቻለ ሲሆን በተደረገው ቆጠራ መሰረት ንብረቶችን በአይነት፣ በጉዳት ደረጃቸውና በአገልግሎት አይነታቸው ከተለዩ በኋላ ወደ አንድ በማምጣት የማዋሀድ ስራ ተሰርቷል።

**ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መለያየትን በሚመለከት**

በአዲስ የተደራጀው የቱሪዝም ሚኒስቴር እና የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም ኮሚቴው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ እና በክፍፍሉ ላይ የምክረ ሃሳብ ቃለ-ጉባዔ በመፈረም ለከፍተኛ አመራር ማቅረብ ተችሏ፡፡ ከፍተኛ አመራሩ የቀረበለትን ምክረ-ሃሳብ መርምሮ እና ተወያይቶበት ውሳኔዎችን ያስተላለፈ ሲሆን መለያየቱ ህጉን ተከትሎ በሰላማዊ መንገድ ተጠናቋል።

**የመዋቅራዊ አደረጃጀት ማሻሻያዎችን በተመለከተ**

አንድ ተቋም የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ያለው የሰው ኃይል ብዛትና ጥራት ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን እንዲሁም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን አዲስ መዋቅር የባለሙያዎች ኮሚቴ በማደራጀት የሰው ሃይል ትመናን ወጭ ቆጣቢ፣ ቢሮክራሲን ያሳጠረና ፕሮፌሽናሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በአመራር ደረጃ ተደጋጋሚ ውይይትና ማስተካከያዎችን በማድረግ ፀድቆ እንዲመጣ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መላክ ተችሏል።

**የዕቅድ ዝግጅት እና ውህደትን በተመለከተ**

የባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ስፖርት ዘርፎች ቀደም ሲል ሲመሩበት የነበረውን የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባርራትን መሰረት ያደረገ እንዲሁም ከተዘጋጀው የሚኒስቴሩ አዲስ መዋቅር አንፃር ለትግበራ አመቺ በሆነ መልኩ የዕቅድ ውህደት መፈፀም በማስፈለጉ የቀጣይ 10 አመታት ዋና ዋና ጉዳዩችን የያዘ የዘርፍ መሪ የልማት እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

መሪ የልማት እቅድ መሠረት በማድረግ በመካከለኛ ጊዜ ተግባራዊ የሚደረግ የ5 አመት ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም በ2014 በጀት አመት ተግባራዊ የሚሆን ዓመታዊ ዕቅድን ከ5 አመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ በመመንዘር የተዘጋጀ ሲሆን እቅዱን ከመላው የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ከባለድርሻ አካላት እንዲሁም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመገምገም እና የጋራ በማድረግ፣ በካስኬዲንግ ስራዎችን እስከታችኛው መዋቅር በማውረድ እና የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል፡፡

## 7) ለክልሎች የተሰጠ የአቅም ግንባታ

በባህል፣ የኪነ-ጥበብ እና ስፖርት ዘርፎችን ዓላማዎች ወደመሬት ለማውረድ በሚያስችሉ ነባር፣ የተሻሻሉ እና አዲስ በተዘጋጁ የአሠራር ስርዓቶችና የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ መድረኮች ተዘጋጅተው አዲስ ለተሾሙ የክልልና ከተማ አስተዳር አመራሮች እና ባለሙያዎች ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን በባህል ዘርፍ በተዘጋጁ የአቅም ግንባታ መድረኮች በኢትዮጵያ የኪነ-ጥበብ፣ ሥነ-ጥበብ እና የፈጠራ ልማት ዘርፍ ፖሊሲዎችና የሕግ ማዕቀፎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናውም የዕደ ጥበብ ልማት አስፈላጊነት

በኢትዮጵያ፣ የኪነጥበብ ሚና በኢትዮጵያ ትናንት፣ ዛሬና ነገ፣ በማደግ ላይ ባሉ አገራት የኪነ-ጥበብና ሥነ-ጥበብ ምንነትና እንደ ብሔራዊ ሀገር ግንባታ ስትራቴጂ የመጠቀም አስፈላጊነት፣ የባህልና ጥበባት ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ፣ የባህል ኢንዱስትሪ ቢዝነስ ተቋማት ቀጣይነት የሚሉ ርእሰ ጉዳዮች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

በስፖርት ዘርፍ በተዘጋጁ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በ2012 ዓ.ም የተጠናው ሀገራዊ የስፖርት ሪፎርም ፕሮግራምን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ጥናቶች፣ የህግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ስርዓት ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን በ13 ሰነዶች ማለትም፡- የስፖርት ሪፎርም ጥናት፣ የአሰልጣኞች ልማት ረቂቅ ማዕቀፍ፣ የኤሊት ስፖርተኞች ልማት ማዕቀፍ፣ የስፖርት ውድድርና ጨዋታዎች ስታንደርድ፣ የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ልማት ፕሮግራም፣ ሃገር አቀፍ የስልጠና ጣቢያዎች፣ ማዕከላትና አካዳሚዎች ማስተግበሪያ ማኑዋል፣ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ልማት የቅብብሎሽ፣ ሽግግርና ዝውውር መምሪያ ሰነድ፣ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ልማት ፕሮግራም የጣቢያ ስታንደርድ፣ የመመዝገቢያ ቋት፣ ፓን አፍሪካን የውድድር ደንብ፣ የተከለሰው የስፖርት ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ እና የስፖርት አዋጅ ሰነድ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

የሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ በህዝባዊ አደረጃጀቶች ውስጥ ለሚገኙ 2,606 የስፖርት ባለሙያዎች በአጭር ጊዜ የስልጠና ፕሮግራም በዳኝነት፣ በአሰልጣኝነት እና ልዩልዩ የሙያ ማሻሻያ የስልጠና ፕሮግራሞች በማሰልጠን ስፖርቱን በብቃት ለመምራትና ለማሳደግ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ተችሏል፡፡

## 8) በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### 8.1.ያጋጠሙ ችግሮች

### 3. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

#### 3.1. ያጋጠሙ ችግሮች

- ☞ ስራዎችን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል ፈጻሚውን እና አስፈጻሚውን ሊያሰራ የሚችል ምቹ የሆነ ቢሮ አለመኖሩ ፤
- ☞ የሚጠየቁ ጥቅል ግዥ ማዕቀፎች በወቅቱና በተጠየቀው መሰረት አለመሟላት

- ☞ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ እና አለመረጋጋት ችግሮች በሁሉም ፕሮግራሞችና በስፖርት ልማት ፕሮግራም ስራው አሉታዊ ተግዳሮት መፍጠሩ፣
- ☞ በካፒታል ፕሮጀክቶች በኩል የብሔራዊ ስታዲየም የምዕራፍ ሁለት ግንባታ የዉጭ ምንዛሬ ክፍያ እና በግብአት አቅርቦት ዓለም አቀፍ የገቢያ ዋጋ ንረት መፈጠሩ፣
- ☞ የብሔራዊ ስታዲየም የሁለተኛዉ ምዕራፍ ግንባታ የቴክኖሎጂ ገጠማ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገራት ላይ በአሳደረዉ ተጽዕኖ ምክንያት ከዉጭ ወደ ሀገር ዉስጥ ለመስገባት መጓተትን መፍጠሩ፣
- ☞ ምንም እንኳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ችግሩ በከፊል እየተፈታ ቢሆንም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ክትትልና ድጋፍ ለመድረግ የተሽከርካሪዎች (መኪና) እጥረት ሙሉ ለሙሉ ያለመቀረፉ፣
- ☞ በብሔራዊ ስታዲየም ዙሪያ የሚገኙ ህገ ወጥ ሰፋሪዎችን ሙሉ ለሙሉ ማስነሳት ያለመቻሉ፣
- ☞ በአንዳንድ ሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ደረጃ የሚታየዩ ቅሬታዎች ውጤት ማጣት የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣
- ☞ በብሄራዊ ስታድየም ጋር ተያይዙ በግቢው ውስጥ የሚገኙ  ህገወጥ ወራሪዎች አለመነሳት (መስጊድ ወ.ዘ.ተ)
- ☞ በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ እየተገነቡ የሚገኙ ስታድየሞች አፈፃፀም ደረጃ ማነስ (ከበጀት አንፃር)
- ☞ ስታድየሞች የአለም አቀፍ ስታንዳርድ ያለማሟላት ችግር በመኖሩ በሃገራችን ውድድር እንዳይካሄድ እገዳ መጣሉ፣
- ☞ በክልሎች ወጥ የሆነ አደረጃጀት አለመኖር፣
- ☞ የሚኒስቴሩ የስራ ክፍሎች፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት እንዲሁም ተጠሪ ተቋማት በያዙት ዕቅድ ልክ የተሟላ ሪፖርት አለማቅረብ፣
- ☞ በሀገሪቱ ተከስቶ በነበረው የፀጥታ እና አለመረጋጋት ችግሮች የባህል እና የስፖርት ልማት ስራ እንዲሁም የሪፖርት ቅብብሎሹ ላይ ከፍተኛ ክፍተት መፍጠሩ፣
- ☞ በበላይ አካላት የሚፀድቁ የህግ ማዕቀፎች በወቅቱ ተጠናቀው ለመምጣት ረጅም ግዜ መውሰዳቸው፣
- ☞ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና የሪፖርት ቅብብሎሽ ስርዓቶች ደካማ መሆን፣

**8.2) የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

### 3.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች

- ☞ ባለው የሰው ኃይል በመጠቀም ሥራዎች እንዲከናወኑ ጥረት ተደርጓል፤
- ☞ ከመስክ ውጭ በቢሮ የሚሰሩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ብቻ ተለይተው ተከናውነዋል
- ☞ ባሉትና በተጣበቡ ክፍሎች በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት ሥራዎች ለማከናወን ጥረቶች ተደርገዋል፤
- ☞ የመረጃ ልውውጥ እና የሪፖርት ቅብብሎሽ ስራዎችን በስልክ፣ በኢሜይል፣ በቴሌግራም ለማከናወን ተሞክሯል፣
- ☞ ወጥ የሆነ የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፣
- ☞ የሕግ ማዕቀፎች በፍጥነት ፀድቀው ወደ ስራ እንዲገቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መስራት ተችሏል፣
- ☞ ከመደበኛ የስራ ሠዓት ውጪ የባህልና የስፖርት ልማት ስራዎችን ማከናወን ተችሏል፣

## 9) ማጠቃለያ (Conclusion)

በአለም ላይ በተከሰተው እስካሁን ድረስ ስጋት ሆኖ በቀጠለው አለም አቀፍ የኮረና ቫይረስ ወረርሽን እና በተለያየ ጊዜ በሀገሪቱ እየተከሰተ ያለው የፀጥታና የሰላም መደፍረስ ምክንያት በበጀት በአመቱ በሴክተሩ ለመስራት ከተያዙ ስራዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ አልተከናወኑም፡፡ በተደረገው ጥረት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱ በዋናው መስሪያ ቤት፣ በተጠሪ ተቋማት እና በክልሎች የተከናወኑትን ተግባራት በማካተት የግማሽ አመቱ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ዋና ዋና ተግባራት በግማሽ አመቱ የተከናወኑና ለቀጣዩ ግማሽ አመት ክንውን መልካም መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በየዘርፉ ለመስራት ታቅደው ያልተከናወኑ እና አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተግባራት ያሉ ሲሆን እነዚህን ተግባራት ለመፈጸም እንዲቻል በቀሪ 6 ወራት ውስጥ ተካተው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ የሴክተሩን ተግባር በስኬት ለማጠናቀቅ አመራሩና ባለሙያው ተቀናጅቶ መስራት ስለሚገባው ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ስራ ይካሄዳል፡፡